# ይድረስ

## ለአቶ  ቡልቻ  ደመቅሳ

የኦሮሞ ፖለቲካ ጉዳይ ከትናንንት እስከ ዛሬ በሚል ርእስ የፃፉትን http://ecadforum.com/Amharic/archives/4660/ በጥንቃቄ አንብቤ የሚከተለውን ምላሽ ጻፍኩለዎት።

በተቀዳሚ የተከበሩ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ያጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣን ቀጥሎም የዓለም ባንክ ሠራተኛ የነበሩት ሰውዬ በአሁኑ ጊዜ በጠባብ የጎሣ ስሜት በሽታ ተለክፈው ስለ ነፍጠኛው ሥርዓት ሲቦተልኩ መስማት በጣም ያስተዛዝባል።

ስለምን ብለው ለሚጠይቁት ኢትዩጵያውያን በዝርዝር የማቀርብላቸውን ይመልከቱት። እርስዎ ያቀረቡት ተረት ተረት ዋና ምንጩ የኢትዩጵያ ቅጥረኛ ዋና ጠላቶች እነ ኦነግ፣ ወያኔ፤ ሻዕቢያና ሌሎቹ ከሚነዙት የውሸት ፈጠራ ወሬ ፕሮፓጋንዳ ቀጥተኛ ቅጂ መሆኑን በአጽንኦት አሰምርበታለሁ። ይህም ማለት፤

<< ኢትዩጵያ የምትባል አገር ከአጤ ምኒልክ በፊት አልነበረችም። የሸዋው ምኒሊክ በአውሮፓውያን ኢምፔሪያሊስቶች ርዳታና ትብብር የኦሮሚያን ነፃ የገዳ ሪፑብሊክ ቅኝ ግዛት በማድረግ ከመቶ ዓመት ወዲህ የተፈጠረች ናት።>>

ተብሎ ዘወትር የሚነዛው የነጻ አውጪ ግንባር ተብዬ የዘመኑ ምድረ ቅጥረኛ ባንዳዎች ልዩ መፈክር በመሆኑ ነው።

የኦነግ መሪ ተብዬ ሁሉ እራሳቸውን በራሳቸው ሾመዋል። ሕዝቡ ያልመረጣቸውና ያልወከላቸው የሕዝብን መብትና ጥቅም አስከባሪ በመምሰልና ከኢትዩጵያ የመገንጠልን ጥያቄ የጎሳው ተቀዳሚና ብቸኛ ፍላጎት እንደሆነ አስመስለው በመቀባጠር፤ ያውም በሩቅ ሆኖ ዘወትር ቡራ ከረዩ እያሉ የሥልጣን ወንበር በአቋራጭ ለማግኘት ቋምጠው ሥጋ እንዳየ ድመት ሲቅነዘነዙ ብዙ ዓመታት ሲሆናቸው ለፈጸሙት ወንጀል ተገቢ ፍርዳቸውን እንደሚያገኙ አያጠራጥርም።

አቶ ቡልቻ ወደ ዋናው ቁም ነገር ከመግባታችን በፊት መሠረታዊ ግንዛቤ በአጭሩ ላስጨብጥዎት።

## ፩ ስለ ነገደ ጋላ

በታሪክ የጽሑፍ ሰነድ የጋላ ነገድ በመባል እስከ የደርግ ወታደራዊ መንግሥት ሥልጣን መያዝ ድረስ የዘለቀው፤ በአፍሪቃ የአካባቢውና የዓለም ሀገራት ዘንድ በስፋት የታወቀው፤ የነገዱ ንዑሳን ልዩ ልዩ ጎሳዎችን አጠቃላይ መጠሪያ የሆነው ቃል በአዋጅ ኦሮሞ እንዲባል የታዘዘ መሆኑን መግለጽ ያስፈልጋል። የሚሲዎን ምልምል ጥቁር ፈረንጆች ኢትዩጵያውያንን ልክ እንደ ባሕር ማዶ ጌቶቻቸው "አቢሲኒያንስ" እያሉ በመጥራት በሬው ሳም ወለደ ፀረ-አበሻ በተለይም ፀረ-ዐማራ ጥላቻ ሲያናፍሱ፤ "ጋላ ብለው የሚጠሩን ዐማሮች ናቸው" እያሉ ዘወትር ያነበንባሉ።

በመጀመሪያ ደረጃ አበሻዎች ጋላ የተባለውን መጠሪያ ቃል ያገኙት ከሱማሌዎች ሲሆን በ16ኛው ክፍለ ዘመን አገራቸውን በደፈጣ ወረራና ዝርፊያ አውድሞ ለሰፈረው ጎሳ መጠሪያ መሆኑ ይታወቃል። የቃሉም መገኛ ምንጭ ከሱማሊኛ ጋል እንደሆነ የሊዎ ራይነሽ ጥናትና እ.አአ 1902 ዓ.ም ያዘጋጁት ሱማልኛ መዝገብ ቃላት ያረጋግጣል። ትርጉሙም እንግዳ፤ ባእድ፤ እስላም ያልሆነ፣ ሃይማኖትየለሽ፤ አረመኔ፤ አሕዛብ ማለት ነው። በኢትጵያም የቃሉ ትርጉም በቀጥታ ተመሳሳይ ነበር። ጋላ ሲባል ክርስትና ያልተነሰ ያልተጠመቀ፤ ያልተገረዘ፤ እስላም ወይም አይሁድ ያልሆነ አሕዛብ (አእዋሚ heathen or pagan) በፊት ሕገ ኦሪትን ያልተቀበለ በወንጌል አምኖ ያልተጠመቀ፤ በአንድ እግዚአብሔር መኖር የማያምን፣ ለእንስሳት፤ ለጨረቃ፤ ለድንጋይ፤ ለዛፍ፤ ለውሃ፤ ለፀሐያ ወዘተረፈ ጣዖታት የሚያመልክ ሕዝብ ማለት ነው። በባህሉና ልማዱ መሥረት ጋላን ጋላ ብሎ የጠራውና የሚጠራው የሱማሌ አስላማዊ ጎሳ ነው። የሱማሌ ጎሳዎች እስልምናን አስቀድመው ስለተቀበሉና ከአረቢያ የፈለሱ አረቦች ጋራ ስለተቀላቀሉ እስላም ያልሆነውን ሁሉ ጋላ ብለው ነው የሚጠሩት። ስለሆነም ነው በቅርብ ዘመን የጋላ ባህላቸውን ትተው የእስላምና ሃይማኖትን የተቀበሉት በሐረርጌ የአዳል ወላስማ አርጎባ ምድር ላይ በወረራ የሰፈሩት የባሬንቱ ጋላ ጎሳዎች እራሳችውን ኦሮሞ ብለው አይጠሩም።

ምክንያቱ ኦሮሞ ወይም ጋላ ማለት አረመኔ፤ አሕዛብ ( pagan) መሆኑን ስለሚያውቁት ለመጠራት የሚመምርጡት በጥቅል እስላማ ሲሉ በየግል ማንነተቸው ግን ኢቱ፤ ኖሌ፤ ጃርሶ፤ አኒያ፤ አፍራን ቃሉ ማለትን በመምረጥ ትውልዳቸውንም ከነቢዩ መሀመድ ዘር ግንድ ጋራ ያይዛሉ። እስላም የሆኑት የአሩሲ ጋሎችም እንደ ሐረርጌ ቆቱዎች የዘር ግንዳቸውን የሚቆጥሩት ከነቢዩ መሐመድ ወገን እንደሆነና እ፡ራሳቸውንም ኦሮሞ ብለው እንደማይጠሩ የአይከ ሃበርላንድ ጥናት ያስረዳል። (E. Haberland:*The Galla of Southern Ethiopia* p.785)

በተጨማሪ ስለ ጋሎች ሌላው ታሪካዊ ሰነድ የምሥራቅ አፍሪቃ ታሪካዊ ዜና መዋእል ሁለት ቅፅ ያለው ባረቢኛ ቋንቋ አል ኪታብ አል ዛንጂ (የጥቁሮች መጽሐፍ) አረቦች ሞቃዲሾን መሠረቷት (Und die Araber bauten Mogadishu) በሚል ርእስ ራይንሃርድ ክላይን አረንደት እ.አ.አ 2004 ጋሎች ከአረቢያ የመን እንደመጡና አእዋሚ መሆናቸውንና የጠላታቸውን ቁላ ሰልበው ካላሳዩ በስተቀር ሚስት ማግባት እንደማይችሉ በጀርመንኛ በተጻፈው መጽሕፍ ገጽ 40 ላይ ይመለከቷል። ሱማሌዎችና ጋሎች ከአረቢያ ባሕረ ሰላጤ ምድር ፈልሰው ወደ አፍሪቃ እንደገቡና ጋሎች በመጀመሪያ በበርብራ ሀርጌሳ አካባቢ ሲኖሩ ከነበረብት ስፍራ በአሥረኛው ክፍለ ዘመን

መጨረሻ አካባቢ የሱማሌ ነገድ ከታጁራ ባሕረ ሰልጤ ተነስቶ ስለወጋቸውና ስላባረራቸው ወደ ደቡብ ምዕራብ ያቤናድር አውራጃ የሸበሌ ሸለቆ ሸሽተው በዋቢ ሸበሌና በጁባ ወንዞች መካከል እስከ ዱቡባዊው የባሌ ቆላማ ቦታ የሰፈሩ መሆናቸውን ያስረዳል።

ሱማሌዎች ስለ ጋሎች ከሃርጌሳና በርበራ አካባቢ መኖርና መባረር ዘወትር በአፉ ታሪካቸው ያስታውሱታል። የልዊስ፣ የችሩሊ፤ የሚድሮክ ( 1959) ፤ የሚችል ወዘተረፈ ጥናትም በግልጽ ያረጋግጣል። ታዲያ! ያጋላ ልሂቃንና የጎሰው ነፃ አውጭ ነን ባይ ቅጥረኛ ሁሉ በምን ሂሳብ ነው "ጋላ ብሎ የሚጠራን አበሻ በተለይም አማራ ነው" እያሉ የሚቀዥብሩት? ዐማራ ባለመሆናቸው ሳቢያ ባደረባቸው የዝቅተኝነት ስሜት ዓይነ ሕሊናቸው ታውሮ ማንነታችው ጠፍቷቸው ለምዕራባውያን ዘረኛ ፈረንጅ አጨብጭፕያቢነት አድረዋል።

የኢትዮጵያን ማኅበረሰብ በተለይም የሸዋን ነባር ሕዝብ ታሪክና ስም በማጥፋትና በመወንጀል አዲስ ታሪክ ለመጻፍ እራሳቸውን "ኦረሞ" ብለው የሚጠሩት ጥቂት "ምሁሮች" ፀረ-ኢትዮጵያ ትርኪ ምርኪ አጠናቅረዋል፤ ያጥጠናቅራሉ።

# ፪ ኦርማንያና ኦሮሚያ የፕሮቴስታንቶች ፈጠራ

በ19ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ጀምሮ የጀርመን ፕሮቴስታንት ሚሲዮን ተብዬ ሰላይዎች እነ ዩሐን ክራፍ፣ ኢዘንበርግ፤ ብሉምሃርድ፤ ወዘተረፈ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ማኅበር (Church Missionary Society(CMS)) ተቀጣሪዎች በመሆን የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ለማስለወጥ፤ ጭለማውን አህጉር ክርስትና ለማንሳት በተባለው ሽፋን አፍሪቃን በቅኝ ግዛት ለመቀራመት ለመያዝ አስበው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። በአድዋ የፕሮቴስታንት ማዕከል ለመገንባት ሲጀምሩ ወዲያው ተባረሩ። እነ ክራፍ ከሰሜን ኢትዮጵያ ሲባረሩ በታጁራ በኩል ወደ ሸዋ ገብተው ለአእዋሚ ጋሎች የፕሮቴስታንት ወንጌል ለመስበክ አቀዱ። በመሆኑም ዩሐን ክራፍ የሚከተለውን ጻፈ፤

"During my residence in Shoa I paid particular attention, as I consider them destined by Providence after their conversion to christianity to attain the importance and fulfil the mission which Heaven has pointed out to the Germans in Europe." (J.Lewis Krapf; *Travels*, *Researches and Missionary Labour During an eighteen years Residence...* ( London :1968 ) , 2nd ed. P 72)

ባማርኛ፣

በሸዋ ቆይታዬ ለጋሎች የተለየ ትኩረት ያደረግሁት በእግዚአብሔር ፀጋ ፕሮቲስታንትነትን ከተቀበሉ በኃላ የሠራዊት ጌታ ለጀርመኖች በአውሮጳ ሳሳየው ተልዕኮ መሳካት የተመረጡ እንደሚሆኑ በመገመት ነው።

ክራፍ ዋና መመሪያውን ቀጥሎ እንደለው አመልክቷል።

" As the Romanist missionary said, " Give us China and Asia is ours;" so may we say, " Give us Gallas and central Africa is ours"  " (ያው ገጽ 25)

የሮማ ኮተሊክ ሚሲዎናዊ "ሽንን (ቻይናን) ስጡን እሲያ የኛ ትሆናለች" እንዳለው ሁሉ "ጋሎችን ስጡን ማዕከላዊ አፍሪቃ የኛ ይሆናል" ማለት ይቻላል በማለት ሃሳቡን ሲቀጥል፤

" In my opinion the great advantage to be derived from the succes of this schem will not be so much in the aquisitions which commerce may drive from the Red sea and countries on its shores, as in the extension of European politity and civilization to Arabia, Abessinia, and the whole of South-Eastern Africa. It will weaken Mohamedanism in the land of its birth, Arabia, and on the African coast; tend to supress the Arabian slave-trade, and subjugate East African Heathensim by christianity and its civilisation; and finally open immense and noble regions in Southern Abessinia and among the Gallas to thousands of European emmigrants when America; Australia and Tasmania cease to attract them." ( ibid P.15)

ያማርኛው ትርጉም፣

<<በኔ ግምት የዕቅዱ መሳካት ጥቅም በቀይ ባሕር ዳርቻ የሚገኙትን አገሮች ንግድ መቆጣጠሪያ ማግኘት ብቻ ሳይሆን የአውሮጳን የፖለቲካ የበላይነትና ሥልጣኔ በአረቢያ፤ በአበሻና መላው ደቡብ ምሥራቅ አፍሪቃ ማስፋፋት ነው። ይህም እስልምናን ከትውልድ ቦታው አረቢያና የአፍሪቃ ጠረፎች ያዳክመዋል፤ ያረቦችን ባሪያ ንግድ ይቀነሳል፤ የምሥራቅ አፍሪቃ አረመኔነት በክርስትናና ሥልጣኔው ይዋጋል። ከአበሻ በስተደቡብ በጋሎች መካክል ያለው ውብ ስፍራ ለሽህ አውሮጳውያን ሠፋሪዎች አሜሪካ፣ አውስትራሊያና ታስማኒያ ሳቢነታቸው ሲያበቃ ሰፊ ዕድል ይከፍታል >>

ጋሎችን በፀረ-እስላምነት በቀላሉ ለመመልመል ታስቦ የተጻፈው ሽንገላና ከንቱ ውዳሴ ደግሞ እንዲህ ተብሏል።

"The Gallas living South of Shoa appeared to be numerous, virile people, capable of resisting Muslims onslaughts. They are relatively unaffected by any false religious principles. In a word, they could become the " Germans" of Africa. " (ያው ገጽ 13 መግቢያ )

ባማርኛ ሲተረጎም፤

<<ከሸዋ በስተደቡብ የሚኖሩት ጋሎች ብዛት ያላቸው ይመስላል፤ የስላሞችን የመስፋፋት ወረራ ሊመክቱ የሚችሉ ብርቱ ሕዝብ ናቸው። ባጭር አባባል <u>የአፍሪቃ ጀርመኖች</u> ሊሆኑ ይችላሉ።>>

የሚሲዎን ምልምል ጠባብ ጎሠኞች ፀረ-ኢትዮጵያ ጥላቻ ጥዋት ማታ ድግምት ዋና ምንጩ ይህ ዓይነቱ ዶሮን ሲድልሏት በመጭያኛ ጣሏት የሚሉት ነው። አለበለዚያማ ጀርመኖች እንኳን ከጥቁር ወገን ሊሆኑት ጋሎች ቀርቶ ያውሮፓ ስላቭ ዘርያ ሞስኮቦችን፣ ፖላንዶችን፣ ሰርቦችን፣ ወዘተረፈ ሰው አይደሉም ብለው ይልቁንም ከነርሱ ጋራ በቋንቋና በባሕል አንድ የሆኑትን የጀርመን አይሁዲዎችንና ጅፕሲዎችን ለይተው በጋዝ መፍጀታቸው፤ ይሁዲ ጀርመኖች በጀርመንኛ የጻፉት መጻሕፍት ሁሉ ተሰብስቦ ማቃጠላቸው ጸረ ሴማዊነታቸው ከቶ አይዘነጋም።

በተለይም ደግሞ በአፍሪቃ ናሚቢያ የጀርመን ቅኝ ገዥ ሰፋሪዎች ነፃነት ወዳድ የሐሬሮና ናማ ጎሳዎችን በአረመኔ ሁኔታ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ መፍጀታችው መቼ ይረሳል!

ክራፍ ወደ ሸዋ ተመልሶ እንዳይገባ በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ (1808-1840) ተከለከለ። በዚህ፣ ምክንያት ጉዞውን ወደ ምሥራቅ አፍሪቃ ዛንዚባር ደሴት አምርቶ ከታወቀው ባሪያ ነጋዴ የኦማን ዘርያ የዛንዚባርና የጠረፍ ከተሞች ሱልጣን ጋራ ተወዳጅቶ በ1844 ዓ.ም መኖሪያውን ሞምባሳ ላይ በማድረግ ጋሎችን ከበስተደቡብ በኩል ለማግኝት በተባለው ሰበብ ምሥራቅ አፍሪቃን በጠቅላላው ለእንግሊዝና ለጀርመን ቅኝ ገዥ ተስፋፊዎች ቀዳሚ መንገድ ጠራጊና አሳሽ ከመሆኑም ሌላ ባቀናበረው ሕተታ ጋሎች "ኦርማኒያ" ተብለው እንዲጠሩ አሳሰበ፤

".. as the Gallas have no general name to indicate their nationality or its seat, I propose to include under the desigination of "<u>Ormania</u>" (ያው ገጽ 73 )

ትርጉሙ፣

" ... ጋሎች ለራሳቸውና ለሚኖሩበት አጠቃላይ መጠሪያ ስለሌላቸው "<u>ኦርማኒያ</u>" ተብለው እንዲጠሩ ሃሳብ አቀርባለሁ። "

በዚያኑ ወቅት የክራፍን <u>ኦርማኒያ</u> ፍልሰማ በመቃወም በደቡብና መሓል አገር ቆይተው የተመለሱት የጅኦግራፊ ባለሙያ

ዶክተር ቻርልስ ቴ. ቢክ የተባሉት በሚያዚያ 25 ቀን 1845 ዓ.ም ሎንደን ላይ በተደረገው የፈላስፎች ጉባኤ ላይ "on the countries south of Abyssinia...." (ከአበሻ በስተደቡብ ሰለሚገኙ አገሮች...) በተሰኘ ርዕስ ባቀረቡት ዘገባ ገጽ 96 ላይ ለምን አዲስ ስያሜ ያስፍልጋል? ጋላ የተባለው ቃል ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ያገኘና የታወቀ ሆኖ ሳለ ሌላ ለምን አስፈለገ ብለው ተቃውሚቸውን አሰሙ። የፈረንሳዊው ኤም ዴ አባዲ በበኩሉ የጋልኛ ቋንቋ ኢልሞርሞ ተብሎ እንዲጠራ የሰነዘረውንም ሃሳብ ውድቅ አድርገውበታል።

የጋላ ነገድ ነፃ አውጪ ነንባይና ልሂቃን ጀርመናዊው ክራፍ ያወጣውን ልብ-ወለድ መጠሪያ ስም ኦርማንያን አሻሽለው ማለትም ኦሮሚያ ብለውታል። የኢትዮጵያን ሕዝብና መንግሥት እያሌ ሺህ ዘመናት ታሪክና ሥልጣኔ በመቶ ዓመት ብቻ ወስነዋል። ከወያኔና ሻእቢያ ጋራ ተባብረው "ኦሮሚያ" ተብየ ትልቅ ካርታ በመሳል ከደርግ ውድቀት መልስ ተግባራዊ አድርገዋል።

የጣሊያን ፋሽስት አስካሪ ባንዳ ውላጆች በተካኑት ፀረ ኢትዮጵያዊነት ጥንታዊውን የሸዋ ክፍለ ሃገር አውራጃዎች ያማራ፣ ያርጎባና የጉራጌ፤ የጋፋት እንዲሁም የሃድያ ከምባታ ምድር ሁሉ ለኦሮሚያ ተብዬው ተከልሏል። ይህን በተመለከተ የጋሞ ተወላጅ አቶ አሰፋ ጨቦ ነፍጠኛው ማነው በሚል ርእስ፡ ባቀረቡት ጽሑፍ ስለ ጋላ ወረራ ያገራቸውን ተወላጅ አባ ባሕርይን ጠቅሰው "ኦሮሞ ዛሬ ባሌ፤ አርሲ፤ ሐረርጌ፤ ጅማ፤ ወለጋ ሸዋ፤ ኢሉባቦር የምንላቸውን አካባቢዎች ይዟል።

ዛሬ የሲዳማና ጌዲኦ አውራጃዎች በኦሮሞ መሓል ደሴት ሆነው የሚታዩት በወቅቱ ወረራውን ተቋቁመው ያመለጡት ብቻ ናቸው። ኦሮሞ ወሮ የያዘው ባዶ መሬት አልነበረም። ባካባቢው በጣም የደረጁ መንግሥታትን አጥፍቶ ነው እንጂ። የኦሮሚያ ክለላ ከታሪካው እውነታ ውጭ ነው። ምንጩም የፖለቲካ ብልጠት ወይም ድንቁርና ይመስለኛል። ማስተዋል የጎደለው የጋራ ቤታችን የሚፈልገውን መጠናኛ ጥገና ለማፍረስ ታጥቀው የሚሰሩ ይመስላል" በማለት በትክክል ገልጸውታል።

እንዲሁም የጥንታዊ ሃድያ ተወላጅና የታሪክ ምሁር የተከበሩ አቶ ኃይሌ አርፌቾ ነፍሳቸው ትማር የሚከተለውን አስፍረዋል።

# ፫ የኦነግ ዓላማና ጸረ አበሻ ፕሮፓጋንዳው

የኦነግ ዓላማ በመርሃ ግብሩ እንደሰፈረውና ዘወትር በሚንዛው ፕሮፓጋንዳ ከአበሻ ቅኝ አገዛዝ ነፃ መውጣትና የኦሮሚያ ሪፑብሊክ መመሥረት ነው። ስለዚህ ድርጅት አፈጣጠር የተከበሩ ዶክተር መራራ ጉዴና በሰፊው አሳውቀውናል።

በአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት መልካም ፈቃድ በወለጋ ክፍለ ሀገር ከተሰራጨው የፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን ጸረ ኦርቶዶክስ ምልምል ቅጥረኞች ጥንስስ እንደሆነ ታውቋል። የተማሪው እንቅስቃሴ በጸረ መንግሥትና በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና ውዥንብር ሲተራመስ ቆይቶ በወታደራው ደርግ የሶሻሊዝም ጨንበልና ማድድናገሪያ ሕጋዊነት አግኝቶ የማኅበረሰብ መመሪያ በተደርገበት ወቅት በኢትዮጵያ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም አሁኑኑ ካልተመሠረተ ብለው ጥራዝ ነጠቆች ሁሉ ሲፎልሉና ሲያንባርቁ ከብዙ ድርጅቶች በተለይም ከሁለቱ ከኢጭአትና ከመኢሶን አባላትና ደጋፊዎች የተውጣጡት ሕብረት በመፍጠር ኦነግን በ1977 ዓ.ም፡ መሥርተዋል።

የኦነግ አባላት በብዛት በወታደራዊ ደርግ ተቋማት በጎቡዕ ከቀበሌ እስከ ላይኛው አካል ተሰማርተው በአብዩትና በሶሻሊዝም ሽፋን አድሃሪ፤ ጨቋኝ፤ ትምክህተኛ፤ ነፍጠኛ፤ ፊውዳል እያሉ ጸረ ዐማራ ዘመቻና ቅስቀሳ አከናውነዋል። የቀይ ሽብር ዋና ተዋናይ ሆነው አያሌ ዐማሮችን በያለበት አስፈጅተዋል።

ያማርኛ መጠሪያ የነበራቸውን ጥንታዊ ስሞች በአዋጅ አስቀይረዋል። ለምሳሌ በጥንታዊ ባሌ ክፍለ ሀገር ውስጥ ከጋላ ወረራ በፊት ጀምሮ ፋሲል ተራራ ተብሎ የሚጠራውን ባቱ ተራራ እንዲባል፣ ጋላ ማለት ቀርቶ ኦሮሞ መባልን በአዋጅ አስነግረዋል። ከሁሉም በላይ መላውን የኢትዮጵያ ገበሬ በጅምላ የመንግሥት ጭሰኛ ያስደረገውን፤ የከተማ ቦታና ጭቃ ቤት ሳይቀር ያስወረሰውን አዋጅ ያስወጡት የኦነግ አባላት እንደ አቶ ዘገየ አስፋው የመሳሰሉት መሆናቸው ይታወቃል። የደርጉን የመሬት ይዞታ አዋጅ በተመለከተ አቶ ቡልቻ ለምን ዝምታን መረጡ?

እርስዎ በልጅ እንዳልካቸው መኮንን ጠቅላይ ሚንስርነት የግብርና ሚንስትር በነበሩበት ወቅት ረዳትዎ የነበሩት ሐቀኛው ኢትዩጵያዊ የተከበሩ አቶ በላይ ዐባይ (ነፍሳቸው ትማር) ስስፊ ጥናት አድርገው ከ20 ሄክታር በላይ ሰፋፊ ይዞታ ያለው ምንም ለሌለው ገበሬ በግል ሃብትነት እንዲሰጥ፤ ዘመናዊ ሰፋፊ እርሻ እንዲስፋፋና ተገቢውን ግብር እንዲከፈል ያዘጋጁት ረቂቅ አዋጅ ተሰርዞ በምትክ የኦነግ የኅቡዕ አባላትና የሶሻሊዝም ጨንበል አጥልቀው ወታደራዊ ደርግን ይዘውሩት የነበረው ሃሳብና ምኞት ተግባራው ሆኖ የኢቱጵያ ኢኮኖሚ ተንኮታኮተ።

የወታደራው ደርግ ሶሻሊዝም ሰባኪና የለውጥ ሐዋሪያ ሆነው በያለበት ሲፎልሉ የነበሩት እንደ አቢዩ ገለታ፤ ታደሰ ኢባ፣ ዲማ ነግዎ፤ መኩሪያ ቡልቻ ወዘተረፈ ከደርጉ ፈርጥጠው በውጭ አገር መሽገው ጸረ ኢትዩጵያ በተለይም ጸረ አማራ ጥላቻ መንዛት ለኦሮሚያ ነጻ መንግሥት ምሥረታ ዋና ስልት አድርገዋል። በዝቅተኝነት ስሜት ዓይነ ሕሊናቸው ታውሮ ማንነታችው ጠፍቷቸው ለዘረኛ ፈረንጅ አጨብጭያቢነት አድረዋል። የኢትዩጵያን ማኅበረሰብ በተለይም የሸዋን ነባር ሕዝብ ታሪክና ስም በማጥፋትና አዲስ ታሪክ ለመጻፍ እራሳቸውን ኦረሞ ብለው የሚጠሩት ጥቂት "ምሁሮች" ፀረ-ኢትዩጵያ ትርኪ ምርኪ አጠናቅረዋል። የጋላ ነገድ ኢትዩጵያን ወሮ አልሠፈረም፤ ዓለም ሲፈጠር የነበረ ነባር ነዋሪ ነው እያሉ ተረት ተረት ይተርካሉ። በ"አቢሲኒያንስ" ከመቶ ዓመታት በፊት ቅኝ ግዛት ከመሆኑ በፊት "ነፃ የገዳ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ" እንደነበረ ኦነግና ብጤዎቹ የኅጥና የጎሣ ጠበብቶች አዲስ የወረሞ ታሪክ በመፈልሰፍ ላይ ናቸው።

የኦነግ የውሸት ክምር ትላንት ሻዕቢያና መሰሎቹ የ "ኤርትራ ታሪክ" ብለው ለብዙ ዓመታት ሲያዘንቡት የነበረውና ያሉት የውሸት ጎርፍ የሚቀዱት ከአንድ ምንጭ ነው።

<< አቢሲኒያ ማለት ቋንቋው ትግርኛና አማርኛ የሆነ ባሕሉ ዐማርኛ ትግርኛ የሆነ ታሪኩ የእነዚህ ሕዝቦች ታሪክ ነው። ይህም ማለት የዛሬ የትግራይና ዐማራ ክልሎች ስም ነው። የኦሮሞና የደቡብ ብሔር ብሔረሰብ ሕዝቦች በአቢሲኒያ ቅኝግዛት ተደርገዋል። የኦሮሞ ጥያቄ የኢትዩጵያ ኢምፓየር አፈጣጠር መሠረታዊ ችግር ነው>> በማለት የኦሮሚያ ሪፑብሊክ ለመመሥረትና ፊንፊኔ የኦሮሚያ መዲና እንደነበረችና እንደምትሆን ሌንጮና ብጤዎቹ እንዳሚቀዣብሩት ሳይሆን ዕውነቱ ዛሬም እንደ ትናንቱ የጋላ ሊሂቃን ችግር ሌላውን የኢትዩጵያ ሕዝብ በተለይም የደቡብ፣ የምዕራብና ምሥራቅ ነባሩን ሕዝቡን ጨፍልቆና ጨፍጭፎ፣ አቃጥሎና አባሮ ቀሪውን ባሪያ (ገባሮ) ለማድረግ ያደረባቸው የቅጥረኝነት አባዜ ነው። ይህ ዐይነቱ ቅዠት በመጀመሪያ የፈጠራ ጥላቻ ወሬና እንዲሁም የአዲስ አበባን ሚሊዎን ነዋሪዎች መብትና ነፃነት የሚቃረን ፀረ ዴሞክራሲያዊ አመለካከት ነው። ዳግመኛም የደቡብና መሃል አገር ነባር ሕዝብን ታሪክና ሕልውና መካድ ነው። ከ16ኛው ክፍለ ዘመን የጋላ ወረራ በፊት የአዲስ አበባና አካባቢዋ ምድር የአማራ፣ የጉራጌ፣ የጋፋትና የወላሞ ነው። ወራሪውና መጤ ሰፋሪውስ የጋላ ጎሳዎች ናቸው። ኦነግ አበሻ ማለት ትግሬና ዐማራ ብቻ አያለ ይወሻክታል። በእርግጥ ጋሊኛ ተናጋሪው ባለገር ኩሩ ሕዝብ ኢትዩጵያዊ አበሻ እንጂ ፈረንጅስ አይደለም። በሌላ በኩል ሲታይም ደግሞ የዛሬው የኢትዩጵያ ሕዝብ የቋንቋ ክፍፍል፣ በዘር ላይ የተመሠረተ አይደለም። ለምሳሌ የዛሬዎች የአርሲ ኦሮምኛ (ጋሊኛ) ተናጋሪዎች ብዙዎቹ የሃድያ ተወላጆችን ያጠቃልላል።

የኦነግ አዲስ ታሪክ ፈጣሪዎች ጥንታዊ ታሪክና ሥልጣኔ የለሾቹ የሰሜን ምዕራብ አውሮፓ የ19ኛው ክፍለ ዘመን ዘግይቶ ደረሽ ሞግዚቶቻቸው የአሪያን ዘርያ ተብዬ ዘረኞች በጎሣ ጥናት ባለሙያነት ካባ ተሸፋፍነው በአውሮፓ ሥር የሰደደውን ፀረ ሴማወያን ቅስቀሳ ለኦነግና ብጤዎቹ አገር በቀል ምልምል ያስክናሉ።

እራሳቸውን በራሳቸው ምዕራባውያን በሚል ስያሜ የነጭ ዘርያ የአሠልጣኝነት ተልእኮና የበላይነት ስሜት ለማስፈን በቅጥረኛ ጀሌዎች ተባባሪነት የአፍሪቃንና የእሲያን ሕዝብ በከፋፍለህ ግዛ ስልት ሸንሽነው ጥገኛ የማስደረግ ዓላማቸው እንዳይሰናከል በስውርና በግልጽ የሚያደርጉት ስልት ነው።

የነ ሻዕቢያና ኦነግ ወኪሎችና አፈ ቀላጢዎች ሆነው የውሸት ታሪክና ያበሻ ሕዝብ የጥላቻ መርዛቸውን በተቀነባበረ ስልት ከሚነነዙት ወገኖች ዓይነተኛ ምሳሌዎች ማቅረብ ቢያስፈልግ እንደ ሆልኮምብ ና ሲሳይ /የኢትዩጵያ አፈጣጠር (The invetion of Ethiopia, 1990)፣ ጆን ሶረንሰን የኢትዩጵያ ቅርጸታ / Imaging Ethiopia, 1993 / ፣ የጣሊያናዊው አሌክሳንድሮ ችሩሊ፣ የእንግሊዙ ባስ ባክስተር ወዘተረፈ ሁሉ አፍቃሪ ፋሽሽትና ናዚዎች፣ በጎሣ ጥናትና ታሪክ ሽፋን ድብቅ ከፋፋይ ፀረ ጥቁር አሳባቸወን ነዝተዋል።

ለምሳሌ ዘመናዊወን የወረሞ ምሁር ዶክተር መሐመድ ሐስን በእንግሊዙ ፀረ አበሻ ግሪንፊልድ ተመልምሎ ዶክተር ለመባል ያጠናቀረውን ሐተታ The Oromo of Ethiopia: A History 1570-1860, (Cambhistorical and antridge: 1990) በተሰኘ ርዕስ የተጻፈወን ፀረ ኢትዩጵያ ዝባዝንኪ እንዲሁም ከግሪንፊልዳ ጋራ ተባ፡ ብሮ (Interpretation of Oromo Nationalism, In Horn of Africa vol.3 No. 1980 ) መጥቀስ ይቻላል። የአሰፋ ጀለታን፤ የአቢዩ ገለታን፣ ሞቲ ቢያን የመሐመድ ሐሰን፤ ወዘተረፈ የውሸት ድርሰት ይመለከቷል። (Http://www.oromia.com/ Articles/ Ethiopian-System-of-domination.html ,Nov.2000)

ኦሮሞ መሆንና ለመሆን ታሪካዊና ሥነ ሰባዊ ምርምሮች ( Being and becoming Oromo- Historical and anthropological enquires) በነ ፖል ባክስተር፣ አሌክሳንድሮ ትሩሊዝ ይየተለመደውን የውሸት ትርኪ ምርኪ የያዘ መጽሐፍ ስውድን ኦፕስላ ታትሟል። መሐመድ ሐሰን በዶክተር መባያ ሐተታ ላይ በከፊል ብቻ የጋሎችን ፍልሰት አምኖ የሉባ ወራሪ ጦር አዝማቾችን እነ መልባህ (1522-1530)፤ ሙዳና (1530-1538)፤ ኪሎሌ (1538-1546)፣ ወዘተረፈ. በደፈጣ ውጊያ የኢትዩጵያን አጤ መንግሥት ግዛት በጀግንነት እንደወረሩ ገድለ ውዳሴ ሲጽፍላቸው፣ የኢትዩጵያ አጤዎችን የመከላከል ጦርነት እያጥላላ፣ የፀረ ኢትዩጵያ ጌቶቹና ሞግዚቶቹ ዘወትር ማነብነብን ማለትም "የባሪያ አደንና ፍንገላ አስመስሎ" ጽፏል።

የሚያስገርመው ነገር በጋላ ወረራ ወቅት የዓይን ምስክር ሆነው ድርጊቱን የመዘገቡትን፤ ከጋሞ ሕዝብ ተወላጅ የነበሩት ከትወልድ አገራችው ከጥንታዊ ጋሞ አውራጃ በጋላ ሉባዎች ወረራና ዝርፊያ የተባረሩትን አባ ባሕርዩን እንኳን ሳይቀር ተቃወሟል (በገጽ 1 ይመልከቷል)።

ኦነግና ልሂቃኑ አባ ባሕርይን፤ አጤ ምኒልክንና ያበሻን ሕዝብ ማብጠልጠልና መኮንን ልዩ ሙያ አድርገውታል። በእስካንዴኒቪያ ስዊድን ላይ መሽጎ ፀረ ኢትዩጵያ ፕሮፓጋንዳ ከሚነዙው ወገን እራሱን ሞቲ ብያ ብሎ ባማርኛ *ከውርስ ውሸቶች በስተጀርባ* በተሰኘ ርዕስ ስቶኮህሎም 1999 ገጽ 75 ላይ የሰፈረውን ያገናዝቧል። ጸሕፊው አባ ባሕርይ ለም፡ን የአረመኔ ጋሎችን ልማድና የወረራ ታሪክ ጻፉ ብሎ ይቀሳፍታል።

አባ ባሕርይ ዜናሁ ለጋላ በሚል ርዕስ በግእዝ ቋንቋ በ1585 ዓ.ም እጅግ በጣም ከፍተኛ የታሪክ ሰነድ መዝግበው አቆይተውናል። ለምን አገራችን ወደመች ብሎ በመጠየቅ ያቀረቡት ሰፊ ማኅበረሰባዊ ትንታኔ ፍጹም ወደር አይገኝለትም። በሌላ በኩል ደግሞ ከመረቁ አወጡልኝ ከሥጋወ ጦመኛ ነኝ እንዲሉ የወረሞ ጠባቦችና የጎሣ ነፃ አውጭ ነን ባዩች ሁሉ ሰለጋላ ነገድ በአባ ባሕርይና ሌሎች ኢትዩጵያወያን የተጻፈወን መልካም ነገር ብቻ ዘወትር መጥቀስ ሲወዱ በአንጻሩ ስለ የጋላ ሉባ የየስምንት ዓመት በጎረቤት አገር ሕዝብ ላይ የደፈጣ ጦር ወረራና ቁላ ቆራጭነት፣ ጨካኝ አረመኔነት ድርጊት እንዳይታወቅ በመመኘት "ያቢሲኒያንስ ደብተሮችን ታሪክ ጸሐፊነት አንቀበልም" እያሉ የኦነግ ካድሬዎች ይዘላብዳሉ።

ባሕርይ፡ እንደዘገቡት ጋሎች ሰው፤ ዝሆን፤ አንበሳ፤ አውሬ፤ አውራሪስ ጎሽ ሲገድሉ ትንሽ ቁንጮ ብቻ ትተው ራሳቸውን እንደሚላጩ፤ ምንም ያልገደለና ሰልቦ ግዳይ ያልጣል ሚስት ማግኘት እንደማይችል ነው። ይህ፡ም፡ የጋላ አረመኔ ልማድ በራያና አዘቦ፤ በቦረና፤ በጥሙጋና ከረዩ፤ በጉጂ ጎሳዎች አንድ ወንድ ብልት ሰልቦ ግዳይ ካልጣሉ በስተቀር ሚስት አያገቡም። የወሎና ጥሙጋ ጋላ መጥፎ ልማድ ገበሬ ክርስቲያንን በጠፍ ጨረቃ አድብቶ በመስልብ ግዳይ፡ ጥሎ ሎቲ ማንጠልጠል፤ አማራ ገበሬ የገደለና የሰለበ ለመሆኑ ሁለት ቅጠል ሰክቶ በገበያው ላይ መንጎራደድ የተለመደ መሆኑ ይታወቃል። (አቶ ዞሐንስ መንገሻ: *ኢትዩጵያ አስተዳደርና ፖለቲካ ሂደት* እ.አአ. 1996 ዓም፡ ሎሳንጀለስ ገጽ 13)

በ1930 ዓ.ም የፋሽስት ጣሊያን ወረራ ወቅት የራያና አዘቦ ጋሎች ለጠላት አድረው በኢትዩጵያ ገበሬ ሠራዊት ላይ ያደረሱት ጭፍጨፋና ከቶ አይረሳም።

በተለይም በሸዋ አርበኞችና ተራ ገበሬ ሕዝብ ላይ አረመኔዎች ያደረሱት፣ን እልቂት አልቤርቶ ሳባች ኢትዮጵያ በሙሶሎኒ ስር በተባለው መጽሐፉ በከፊል ጠቅሶታል። በዚያው ዓመት ከጥር ወር ጀምሮ በይፋትና አንኮበር አውራጃ የአርጎባና አማራ ገበሬዎችን በፋሽስት ሰላቶዎችና በውሾቻቸው የኤርትራና ሱማሌ አስካሪ ባንድዎች የአየርና የምድር ጦር እንዲሁም የራያና አዘቦ፤ የጥሙጋ ጋሎች ዘራፊነትና ሰላቢነት ወንድ አዛውንትና ሕፃናትን ሲልበዋል። የባልቴትና ልጃገረዶችን ጡታቸውን ቆርጠዋል። ገዳማት፤ አቢያተ ክርስቲያንና መስጊዶች፤ መኖሪያ ቤቶች ጋይተዋ፤ ከብትና ንብረት በገፍ ተዘርፈዋል። ለምሳሌማ ያህል ዕውቁ ሰአሊ አፈወርቅ ተክሌ በሕፃንነቱ እናቱ ይዛው ስትሸሽ በራያ ጋላ የተሰለበው በዚሁ ወቅት ነው። በደንና ዋሻ ተደብቀው ሕይወታቸውን ያተረፉት፤ ተሰልበው ያልሞቱት የፋሽስቶንና የራያ ጋሎችን አረመኔነት ዘወትር ሲስታውሱት እንደነበር በዘመነ ደርግ የእድገት በኅብረት ዘመቻ ወቅት ገበሬ ሽማግሌዎች ነግረውናል። ያረመኔ ጋላን መጥፎ ልማድና የራያችን የባንዳነት ድርጊት ለመሸፋፈኝ ሲሊ ጋላ አንባልም በማለት ፈረንጅ አምላካቸው የሚላቸውን ፀረ አበሻ ጥላቻ ብቻ እንደ በቀቀን ተግተው ያማራ ጥላቻ ያስተጋባሉ። ነገር ግን ከአበሻዎች ሌላ ያውም በቅርቡ ያውሮፓና እሲያ ስለ የጋላ ሉባ ሰላቢነት የጻፉትን ቀጥሎ ይመለከቷል።

<< The gada System of the Boran provided the rule that each new set initiated into the raaba grade had to go on a rituasl war expidation to procure livestock and the cut off genetials of a male strangers as trophies. As these initiations took place every eight years, the neighbours of the Boran were subjected to a reign of periodic terror.>> ( Eisei Kurimoto, Simon Simones: Conflict, Age & power in North East Africa 1998, p128)

በኢትዮጵያ ጥንታዊ አገርነትና የጥቁር ሕዝብ ሥልጣኔ፤ የግእዝ ፊደልና ሥነ ጽሑፍ መኖር የሚቀኑት ዘረኞች እንደ ግሪንፊልድ፣ ባክስተት፤ ጆን ማርካኪስ ወዘተረፈ የመሳሰሉት አገር በቀል ምልምሎችን አዘጋጅተው አሰማርተዋል። የኦነጉ ኣዲስ ታሪክ ፈጣሪው መሀመድ ጌቶቹ በጥቁር ሕዝብ ጥላቻ ያጠናቀሩትን መልሶ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው መጽሐፉ ሲያቀነቅን

" ... They ("Abyssinians") played down their Africaness. Christian and Negro were often cited as opposite, as good and evile. Oromo or Galla as it was called, derived from Africa.." (ገጽ 3)

ትርጉም፣

<< አበሾች ጥቁር አፍሪቃዊነታቸውን አይቀበሉትም። ክርስትናና ሻንቅላነት እንዲሁም ጽድቅና ኃጢአት በተቃራኒነት ዘወትር ይጠቅሳሉ። ጋላ ከጥቁር አፍሪቃ የተገኘ ነው።>>

ይህማ ምነም አዲስ ግኝት ሳይሆን ዘረኛ ነጮች የጥቁር ሕዝብ ወገንን ሁሉ በዓለም ዙሪያ በብቸኛይቱ ነፃ የጥቁር ሕዝብ መንግሥትና ምሳሌነት እንዳይኮሩና ፀረ ቅኝ ግዛት ትግላቸውን አጋር ለማሳጣት ታስቦ በጥንቃቄ ያቀናበሩት የውሸት ስብከትና ማወናበጃ ነው። ምዕራብ አውሮፓውያን አፍሪቃን ተቀራምታው፣ የጥቁርንና የሰሜንና ደቡብ አሜሪካ ቀይ ሕዝብ ዘርያዎችን በዝቅተኛ ደረጃ መድበው ከየቅኝ ግዛታቸው ሁሉ ናሙና በማስመጣት በአውሮፓና ሰሜን አሜሪካ ትልልቅ ከተሞች ውስጥ በሚገኙት ቤተ እንሳሳት ( Zoological garden) የአርመኔዎች ትዕይንት / Savage show/ የተባለው ከ1870-1933 ድረስ ይታይ ነበር። በዚህም መሠረት ጥቁሮች ከዝንጀሮ ጋራ ለእይታ በሚቀርቡበት አፍላ ወቅት ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጤ ምኒሊክ መሪነት ከዳር እስከ ዳር ተባብሮ ከፍተኛ ድል በአድዋ ጦር ሜዳ በአውሮፓ ነጭ ዘመናዊ ወታደር ላይ ድል የተጎናጸፈው። ምድረ ዘረኛ አበሾች ጥቁር አፍሪቃውያን አይደሉም፤ ከእሲያ የመጡ ናቸው አያሉ ለሽንፈታቸው ሰበብ የፈለጉትና የውሸት ድር፡ሰት ያጠራቀሙት። በዓለም ዙሪያ የነፃነት ወዳዱን ሕዝብ መነሳሳትና የጸረ ቅኝግዛት እንቅስቃሴን ለመግታት፤ የኢትዮጵያን አርአያነት ዋጋ ለማሳጣት አስበው ነው አበሾች ጥቁር አፍሪቃውያን አይደሉም እያሉ ጸረ ኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳ በሰፊ የነዙትና ለበቀል ርምጃ የተዘጋጁት። "ኢትዮጵያውያን ጥቁር አፍሪቃውያን አይደለንም ይላሉ" እየተባለ የምዕራቡ ዓለም ዘረኞች ፀረ ኢትዮጵያ ቅጥፈትን ቅጥረኛው ኦነግ ሰምቶ ያራግባል።

ከአድዋ ድል መልስ ኢትዮጵያውያን ጥቁር አፍሪቃውያን ሆነን እንዳልሆንንና ከአረቢያ ሠፋሪዎች ዝርያ ወገን በመመደብ የጥቁር ሕዝቦችን ሕብረትና አንድነት ለያይቶ ለመግዛት ከተሸረበው ስልት አንዱ ነው። የ"ኦሮሞ" ነገድ አፈቀላጤ ነኝ ባይ ጆን ሶርንሶን ይህንኑ ስልት ሲያናፍስ "የአበሻ ምሁራን አፍሪቃዊ ማንነትን ክደው ከጥንት ዕብራውያን ጋራ በሰሎሞንና ንግሥተ ሳባ በኩል ሳላቸው ግንኙነት ትኩረት ይሰጣሉ። የአበሻ የጽሑፍ ታሪክ ኦሮሞዎችን ያገለለል ነው" በማለት ቀባጥሯል። (Crisis and Terror in Horn of Afrcia,USA P 41)

በ16ኛው ክ.ፍ.ዘ ጋላ በአገራችን ወሮ ከሰፈረና ከተዋሃደ ወዲህ ያለውን ማኅበራዊ ክንውን በሚገባ ተመዝግቧል። ነገር ግን ያምዕራብ አውሮፓ ምድረ ዘረኛ ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ፤ ባሕል፤ ቋንቋ፤ ሥልጣኔ ብቸኛ አዋቂ ነንን ያሉት ኢትዮጵያን ከአፍሪቃ አህጉር ነጥለው ከመካከለኛው ምሥራቅ ጋራ በማቆራኘት የአክሱምን አፍሪቃዊ ሥልጣኔ ሥር መሠረት ክደውና ዘመኑንም አሳጥረው የየመን አረብ ሰፋሪዎች ፈጠራ ነው እያሉ ይለፍፋሉ። አፍሪቃ ታሪክ የለሽ ሌጣ ወረቀት ነው እያለ የጀርመኑ ፈላስፋ ትብዬው ሄግል ወሻክቷል። የጥንት ግብፃውያንና ኢትዮጵያውያን በአፍሪቃ አባይ ሸለቆ ሥልጣኔን የጀመሩ፤ በዘር፤ በሃይማኖት፤ በቋንቋ፤ በባሕል አንድ የነበሩ ጥቁር አፍሪቃውያን መሆናቸውን ዘረኞች ሸፍጠው ከአፍሪቃ ውጭ ከሌላ ቦታ የመጡ በማስመሰል ያወናብዳሉ። ያበሻን ጥቁር ሕዝብ ሴማዊና ካማዊ እያሉ ከፋፍለዋል።

ያይጥ ምስክሯ ድንቢጥ እንዲሉ የጸረ ኢትዮጵያው የሶርንሶን ሃሳብ የኦነጉ አቢዩ ገለታ የደርግ ባለሥልጣን የነበረውና ቀጥሎም የኦነግ የውጭ መምሪያ ሃላፊ የእበሻ ሕዝብ ጥላቻ ቅስቀሳ <u>የኢትዮጵያ መጨቆኛ ሥርዓትና ውጤቱ</u> (Ethiopian System of domination and consquences) በሚል ርእስ የመለኮታዊ መብት የመጨቆኛ ምሳሌ ከሶርሰንና ብጤዎቹ ፀረ ሴማውያን የተነገረውን እንደ በቀቀን ሰምቶ ያስተጋባውን እንጠቅሳለን።

<< ... Menelik had to seek acceptance by European powers as a partner during the era of Africa. To claim legitimacy based on antiquity and divine authority of biblical proportion, the Abyssinians gave their empire the name " Ethiopia". There also emerged a racist belief that " they have a much higher form of intellegence than the purly Negro peoples of Africa." (htt://www.oromia.com/Articles/Ethiopian_system_of_domination_and_ consequences)

ትርጉሙ፣

ምኒልክ ከአውሮፓ ኃይሎች ጋራ በአፍሪቃ ቅርጭያ ዘመን እንደ ተባባሪ እውቅና ለማግኘት መፈለግ ነበረበት። በጥንታዊነትና በመጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ ሥልጣን አለኝ ማለት አበሾች ለግዛታቸው ኢትዮጵያ የሚል ስም ሰጥተዋል። እነሱ ከንጹሕ የአፍሪቃ ጥቁሮች እጅግ በጣም የላቀ ብልኅነት አላቸው የሚል የዘረኝነት እምነት ተፈጥሯል። >>

ይህ ዓይነት የቅናት ወሬ የተቀናበረው በችኮ መንቻካ የነጭ ዘር የበላይነት አናፈሾች መሆኑ ግልጽ ነው። ውሻ በበላበት ይጮኻል እንዲሉ የኦነግ ድርጎኞች ለእንደዚህ ያለ ተራ ቅጥረኝነት ዓይናቸውን በጨው አጥበው፣ በኢትዮጵያዊነት ጭፍን ጥላቻ ተክነው፣ አበሻ ባለመሆናቸው እጅግ በጣም በቁጭት በሽታ ሕሊናቸውን የሳቱና የኢትዮጳያ ሕዝብና መንግሥት የረጅም ዘመናት ታሪክና ሥልጣኔ የዐማራው ብቻ እንደሆነ ተደርጎ የተነገራቸውና፣ የሚመስላቸው ወገኖች፣ በፀረ ሴማውያን ያውሮፓ ዘረኞች የከሰረ ርዕዩት የተመለመሉና የተካኑ ናቸው። ላውሮፓ ዘረኞች የኢትዮጵያ መንግሥት በአባይ ሸለቆና ቀይ ባሕር ዳርቻ መኖር የረመጥ እሳት፣ ያይናቸው ውስጥ ጉድፍ ሆኖባቸው ቆይቷል። በመሆኑም ሕዝቡን በጎሳና በሃይማኖት ከፋፍሎ በማቃረን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ከአልተቻለም ለማዳከም የሚቻለው ኢትዮጵያዊነት ወድሞ ጣባብ ጎሰኝነት ሲሰፍን ብቻ እንደሆነ ተግንዝበዋል። ስለሆነም ላንዱ ቋንቋ ተናጋሪ ጠበቃና ሞግዚት፣ አዛኝ ቅቤ አንጓች ሆነው ይቀርባሉ። ታማኝ ቅጥረኛ መስሎ ለታያቸው ውዳሴ ከንቱ ይደረድሩለታል። የገዛ ወገኑን፣ ወንድሙን እንዲጠላ ይቀሰቅሱታል። ቅኝገዥዎች ኢትዮጵያን ለመያዝ የጎሰኝነት እሳት በማቀጣጠል ብቻ ይሳካልናል ብለው ኅምኸተዋል። ጠባብ ጎሰኞችም ሥልጣን በአቋራጭ ይዘው ለመበዝበዝና ለማስበዝበዝ ይቋምጣሉ።

ከተጨባጩ ሁኔታ አንጻር ጋሎች ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ በኢትዮጵያ ምድር ከሠፈሩበት ጊዜ ጀምሮ የተደረገው መስተጋብር ተጽፏል። ከዚያ በፊት የኢትዮጵያ ዜጋ ሳይሆኑ አበሾች ለምን ስለ ነገደ ጋላ አልጻፉም ከተባለ ተገቢው ጥያቄ ለምን ሁሉን ነገር አዋቂና ሥልጡን ነኝ ባዮች ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ስለ "ኦሮሞ" ለምን ጽፈው አላቆዩም? አውሮፓ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን በፊት በጭለማ ኑሮ ይዳክር ስለነበር እንኳንስ ስለ ነገደ ጋላ ታሪክ ሊጽፉ ይቅርና ከምዕራብ አውሮፓ ሌላ ምድር መኖሩን እንኳ ፍጹም የማያውቅ፣ መሠልጠንም የጀመረው በሴማውያን ይሁዲ ሰፋሪዎችና ከእስላም አረብ ሥልጣኔ በመቅዳት ነው።

የመካከለኛው ምሥራቅ ጥንት ነዋሪዎች ዕብራውያን፣ ሱማሪያን፣ አረቦች ወዘተረፈ ሁሉም የነጭ ሕዝብ ዘርያ አይደሉም። የጠይም ቀይና ጥቁር ዘርያ ነበሩ እንጂ። በዓለም ታሪክ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በአፍሪቃዊነቱ፣ በጥቁርነቱ፣ በነፃነት ወዳድነቱ ከመኩራቱ በስተቀር ከቶ ምንም ግዜ ከነጭ የፈረንጅ ወገን ነኝ ብሎም አይውቅም። በተለይ የሰሜን አሜሪካ የአውሮፓ ሰፋሪ ቅኝገዥ ወራሪዎች የአንግሎ ሳክሶን የነጭ ዘር ላዕላይነት ስሜት አራጋቢዎች ኢትዮጵያውያን ኔግሮ አይደለንም ይላሉ ብለው ከአፍሪቃ በባርነት ቀንበር ሰርቀው ላሻገሩዋቸው ጥቁር አሜሪካውያን በሰፊው የወሻክቱላቸው እንደነበር ታዋቂው የነፃነት ታጋይ ማልኮልም ኤክስ አፍሪቃን ሲገበኝ አዲስ አበባ ደርሶ ከተመለሰ በኋላ የተገነዘበውን እዚህ ላይ መጥቀሱ ሁኔታውን ግልጽ ያደርገዋል።

" So, I went through khartoum to Addis Ababa, Ethiopia, which is a wonderful country. It has its problems, and it's still a wonderful country. Some of the most beautiful people I've seen are in Ethiopia, and most intellegent and most dignified, right there in Ethiopia. You hear all kinds of propaganda about Ethiopia. But any time a person tries to tell you as they've told you and me, that Ethiopians don't think they're the same as we are, that's some of that man's manufacturing. He made that up ...They are just as friendly towards us as anybody else is." (G. Breitman; By any means Necessary, (London: 1985), p. 142)

ትርጉሙ፣

ከካርቱም ወደ አዲስ አበባ ውብድንቅ ከሆነችው አገር ኢትዮጵያ ተጓዝኩ። የራሷ ችግሮች ቢኖራትም ውብ ድንቅ አገር ናት። ካየኋቸው እጅግ በጣም ቆንጆ ሰዎች በኢትዮጵያ ናቸው፣ በጣም ብልሆችና የተከበሩትንም በዚያው በኢትዮጵያ ነው። ስለ ኢትዮጵያ ሁሉንም ዓይነት ፕሮፓጋንዳ ትሰማላችሁ።

ሰውዬው ዘወትር ሊነግራችሁ እንደሚሞክረው፣ ለኔ ለናንተም እንድነገሩን ኢትዮጵያውያን እንደኛ እንደሆኑ አያስቡም፣ ይህስ ያ ሰው ከፈጠረው ጥቂቱ ነው። ውሸቱ ነው።.. እንደማንኛውም ሌላው ሁሉ እነሱ ለኛ ወዳጆቻችን ናቸው

በምድረ አሜሪካ ዘረኝነት ድርጅታዊ ቅርፅ ነበረው፣ አለው። ጥቁር አሜሪካውያን ፀረ ዘረኝነት ታጋዩች የአሜሪካንን ድርጅታዊ ዘረኝነት ሲያገናዝቡ "ኔግሮ" ለሚሉት ቃል ዘረኛ ነጮች የሰጡት ትርጓሜ ታሪክ፣ ሥልጣኔ፣ ባሕል፣ ሃይማኖት የሌለው፣ በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ፣ በቻርለስ ዳርዊን የዝግም ለውጥ ሂደትን ገና ያልጨረሰ፣ ምንጩ ከጨለማው አህጉር አፍሪቃ በምዕራብ አውሮፓ የባሪያ ፈንጋዮች ማለት በፖርቱጋሎች፣ በእስፓኞች፤ በእንግሊዞች፣ በሆላንድና ሌሎች ለተሠረቁት ጥቁር ሕዝቦች መጠሪያነት የተሰየመ ሰለሆነ ምንም ዓይነት ተቀባይነት እንደሌለው በማመልከታቸው ዛሬ "ኔግሮ" የተባለው ቃል ውድቅ ተደርጎ ጥቁር አሜሪካዊ ወይም አፍሪቃ አሜሪካዊ (African American) እየተባለ መጠራት ተጀምሯል።

ታዲያ ኢትዮጵያውያን ጥንትም፣ ዛሬም ለወደፊቱም ጥቁር አፍሪቃውያን ነበርን፣ ነን እንጂ ያውሮፓ ዘረኛ ስያሜ የንቀትና የጥቁር ጥላቻ መጠሪያ ቃል "ኔግሮ" አስቀድመን አለመቀበላችን በዓለም ጥቁር ሕዝብ ዘርያዎች ዘንድ ያኮራናል። በቅኝ ተገዥነት ቀንበር ስር ለወደቁት ሁሉ መመኪያ የነፃነት ጮራ ፈንጣቂ ኮከብ አስደርጎናል። በመሆኑም ዘረኞችና ምንደኞቻቸው ፀረ ኢትይጵያ የፈጠራ ወሬ ቢያናፍሱ አያስገርምም። ታላቁ አርብኛ የመጀመሪያ ኢትዮጵያዊ ሐኪም ዶክተር መላኩ በያን የአሜሪካና ካሬቢክ የጥቁር ሕዝብ ዘርያዎችን ሁሉ በማስተባበር ፀረ ዘረኝነት፣ ፀረ ፋሽሽት ትግሉን ከታላቋ እንግሊዛዊት ወይዘሮ ሲልቪያ ፓንክረስት ጋራ በመተባበር አከናወኗል።

ዶክተር መላኩ ነው ከሁሉ አስቀድሞ "ኔግሮ" የተሰኘ የነጭ ዘር የበላይነት ስሜት አራጋቢዎች ያወጡትን መጠሪያ ቃል በመቃወም ጥቁር አሜሪካዊ ተብለው እንዲጠሩ ያሳወቀው።

በፋሽሽት ጣሊያን አረመኔ ወረራ ከ1928 እስከ 1933 ዓ.ም ጥቁር አሜሪካወያን ከኢትዮጵያወያን ወገኖቻቸው ጎን በመቆም ይልቁንም ባሜሪካ ታላላቅ ከተሞች ለምሳሌ በኒዩርክ ሀርለም፤ በፔንሲልቫኒያ ወዘተረፈ. ያደረጉት ጸረ ፋሽሽት የተቃወሞ ሰልፍ ዘወትር ይታወሳል። የጣሊያን ዘርያ ያላቸው አሜሪካዊ ተብዬ ድቅልቅል ወላጆችዎች ደግሞ በዱቼ ሙሶሎኒ ማጓራትና የጥቁር ሸሚዝ ካድሬዎቹ የአበሻን ጥቁር ሕዝብ አረመኔ ጭፍጨፋ በመደገፍ ፈንጠዝያ ሲያደርጉ ጥቁር አሜሪካወያን ሱቆቻቸወንና የንግድ ድርጅቶቻቸወን መሰባበራቸው ተመዝግቧል (Peter Alexander et al. 2000, PP. 18-23)።

ያውሮፓ ዘረኞች የጥንት ግብፅ ጥቁር ሕዝብን ታሪክና ሥልጣኔ ከአፍሪቃ አህጉር ለይተው የአውሮፓና እሲያ ነጭ ሠፋሪዎች ፈጠራ እንድሆነ አስመስለው እንደዋሹት ሁሉ የኢትዮጵያንም ጥቁር ሕዝብ ሥልጣኔ ታሪክ፣ ባሕል፣ ፊደል፣ ሥነ ጽሑፍ በጠቅላላወ ከአፍሪቃ ወጭ ከአወሮጳና ከእሲያ የመጡ "ነጮች ፈጠራ ነወ" እያሉ ቀዣብረዋል።

# ፬ በኢትዮጵያ ባሪያ ፈንጋና ነጋዴዎች እነማን ነበሩ የባሪያ ሥርዓት የነበረው የት ነው?

ከአጤ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት 200 ዓመታት በፊት በምሥራቅ፣ በደቡብና በምዕራብ ኢትዮጵያ የነበረውን ሁኔታ በማገናዘብ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ "<u>አጤ ምኒልክ ኦሮሞን የገዙበት የባሪያ አገዛዝ ሁለት እርምጃ ወደ ኋላ እንዲሄድ አድርጎታል።"</u> በማለት የቀባጠሩትን የፈጠራ ወሬ ማጋለጥ አስፈላጊ ነው።

በተቀዳሚ የምኒሊክ ሠራዊትና መኳንንት የሸዋ ተወላጆች ናቸው። ሸዌዎች ደግሞ ተጉለቴዎች፤ ይፋቶች፤ ጉራጌዎች፤ መንዜዎች፤ መራቤቴዎች፤ ከምባታዎች፤ሞረቴዎች፤ አብቱዎች፤ ሃድያዎች፤ ገላናዎች፤ በቾዎች፤ አዳበርጋዎች ሰላሌዎች፤ አርጎባዎች፤ አፋሮች፤ ወዘተረፈ ክርስቲያንና እስላም የሆኑ የሸዋ ዜጎችን ያጠቃልላል፣

ሌላው የወሬ ማጣፈጭያ አጤ ምኒልክ ከአውሮፓ ቅኝገዥ ተስፋፊዎች ብዙ የጦር መሣሪያ ስላገኙ ነው የኦሮሚያን የገዳ ነፃ ሪፑብሊክ ለመያዝ የቻሉት እየተባለ የሚወሻከተው ነው። ለምን ታዲያ! ወለጋዎች፤ ጅማዎች፤ የሐረርጌ ቆቱዎች፤ አሩሲዎች፤ ጉጅዎች፤ ቦረናዎች ወዘተረፈ ጦር መሣሪያ አላገኛችሁም? ማንስ ከለከላችሁ?

የኦነግ ፕሮፓጋንዳ አቀናባሪዎች የአበሾች መንግሥት በተለይ የአጤ ምኒልክ ክርስቲያን ስልሆኑ ያውሮፓን ክርስቲያን ተብዬዎችን ርዳታና ትብብር አግኝተዋል እያሉ ማደናገሪያ ወሬ ያናፍሳሉ። ይህም የምዕራብ አውሮፓ ፈረንጆች ለአበሻ ጥቁር ሕዝብ በአፍሪቃ ይረዳሉ ማለት አንድም ድንቁርና ወይም በቅጥረኝነት በል ተብለው የተነገራቸውን መልሶ ማስተጋባት ነው።ለምን የአድዋው ጦርነት ተደረገ? ለምን የኮተሊኮችና ፕሮቴስታንት ሚሲዎኖች የግብፅን እስላማዊ ተስፋፊ የእንግሊዝ ጥገኛ መንግሥትን ረድተውና ደግፈው ጸረ አበሻ ሴራ ጎነጎኑ? ወራሪ ጦር አዝምተው በታላቁ ጀግና አሉላ አባ ነጋ ድባቅ ተመቱ?

ይልቅስ ስለ ነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ቀጥሎ የቀረበውን በአጭሩ መምልከት ጉዳዩን ግልጽ ያደርገዋል።

የኦስማን ቱርክና ግብፅ ሎሌና ዋና ባሪያ ነጋዴ የነበረው የሐረሩ ኢሚር አብዱላሂ ከእንግሊዞች ጋራ ተመሳጥሮ የሠለጠኑ ወታደሮችና ብዙ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ጠመንጃና መድፎች አግኝቶ ነበር። በዚያን ወቅት እንግሊዞችና ጣሊያኖች ሐረርጌን የቅኝ ግዛታቸው አካል ለማድረግ በከፍተኛ ደረጃ ይሽቀዳደሙ ነበረ። ማንም ማወቅ ያለበት ሐቅ አለ። ይኸውም የአዳል ሡልጣናት በጠቅላላው ከዋና ማዕከሉ ሐረር ከተማ እስከ ዘይላ በርበራ ሕንድ ውቅያኖስ ድረስ የኛ ጥንታዊ ክፍለ ሀገር ነው። በመሆኑም አብዱላሂ በሰላም እጅ እንዲሰጥና እንደ ጥንቱ እንዲገብር ተጠየቀ። እሱ ግን "ለካፊር አልገብርም" ብሎ ለጦርነት ተዘጋጀ። ጨለንቆ ላይ ከአደሬዎችና ቆቱዎች አስላማዊ ሠራዊት ጋራ በተደረገው የሩብ ሰዓት ጦርነት አብዱላሂ ከእንግሊዝ የተሰጠውን ዘመናዊ መድፍና ጠመንጃ ሁሉ ለሸዋ ሠራዊት አስረክቦ ሸሸ። ከድል መልስም እንኳ ምህረት ቢደረግለትም እንኳ ሌሊቱን ከሐረር ወደ ጅጅጋ ፈርጥጦ አገር ጥሎ በመጥፋት ዛንዚባር ገባ። የሐረር ከተማ ያለምንም ደም መፋሰስ፤ ያለምንም ዝርፊያና ውድመት በጀግናው የሸዋ ሠራዊት መያዙዋን ዓለምን ያስደንቀ መሆኑን የታሪክ መዛግብት ያመለክታሉ።

ግብፃውያንና ቱርኮች በሃይማኖት ሽፋን ወዳጅ፤ በዘርና በባሕል አንድ የሆኑት ኢትዮጵያውያን አጤዎች ክርስቲያን በመሆናቸው ምክንያት ተስፋፊና ቅኝ ገዥ ሊባሉ አይገባም። አቶ ቡልቻ ስለባሪያ ያነሱ ስልሆነ ዝርዝሩ ይኸው።

## በኢትዮጵያ ባሪያ ፈንጋይና ነጋዴዎች እነማን ነበሩ?

በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የክርስቲያን ልጅን ለባርነት የሸጠና ያሸጠ ክርስቲያን ዜጋ በፍትሐ ነገሥት የሞት ፍርድ በስቅላት ይፈረድበት እንደነበረ የፕሮቴስታንት ሚሲዎን ተባይ እነክራፍ ሸፈጠዋል። በገብር አልገብርም የሥልጣን ሽሚያ ጦርነት የሚማረኩትን ሁሉ "ባሪያ" አድርገው ቆጠረዋቸዋል። ነገር ግን በአገራችንም ሆነ ሌሎች አገሮች የጦር ምርኮኞች ሁሉ በነገሥታቱና መኳንንቱ ቤት ክርስትና ተነስተው፣ የቤተሰቡ አባል ሆነው ከልጅና ሥጋ ዘመድ እኩል እንደ ሥራቸውና አገልግሎታቸው መጠንና ትጋት ቤትና ንብረት፣ ርስት እንኳ ሳይቀር ይወርሱ እንደ ነበር የተረጋገጠ ነው። መቸም ፈረንጆች በጅምላ ዋሾችና ዘረኞች፣ አጭበርባሪና ጉረኞች አይደሉም። እንደ ሄንሪ ሶልትና ጆን ከምዴን የመሳሰሉትን ሐቀኞቹ በትክክል ያዩትንና የሰሙትን መዝግበዋል።

በ19ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ገደማ ሄንሪ ሶልት የተባሉት ኢትዮጵያን ጎብኝተው ስለባሪያ ንግድ ሁኔታ ቀጥሎ ያለውን መዝግበዋል።

The situation of slaves is rather honourabel than disgraceful and the difference between their state and that of western slaves is strictly apparent. They have no long voyage to make, no violent change of habits to undergo, no outdoor labour to perform, no white mans scorn to endure, but on the contrary are frequenly adopted like children into the family. (Salt, 1814 p.382)

ባማርኛ ሲመለስ፣

የባሮች ሁኔታ የሚያሳፍር ሳይሆን የሚይስክብር ነው። በምዕራቡ ዓለም ከሚገኙት የባሮች ሁኔታ በፍጹም የተለየ ነው። ትልቅ ጉዞ የለባቸውም፣ ልማዳቸውን በኃይል ለማስለወጥ አይገደዱም፣ ከቤት ውጪ ሥራ የለባቸውም፣ የነጭ ሰውን ቁጣና ግልምጭያ ተሸካሚ አይደሉም፣ በተቃራኒው እንዲያውም አብዛኛውን ጊዜ እንደ ጉዲፈቻ ሕፃናት የቤተሰብ አባላት ይደረጋሉ።

በመላው አፍሪቃ የባሪያ ንግድ ተደርጓል። በሰሜንና ምሥራቅ ከግብፅ እስከ ሞዛምቢክ ድረስ በጠረፍ ዳርቻች ለምሳሌ ምጽዋ፣ ታጁራ፣ ዘይላ፣ በርበራ፣ መቃዲሾ፣ ማሊንዲ ሞምባሳ፣ ዛንዚባር፣ ዳረሰላም ወዘተረፈ, ለቱርክና አረብ ባሪያ ገባያ ማቅረቢያ ጣቢያዎች ነበሩ። ነጋዴዎቹም ይሁዲዎች፤ አረቦችና የአካባቢው ተወላጅ እስላሞች እንደነበሩ ይታወቃል።

<u>ጀብርቲ</u>ና ውርጂ ተብለው የሚጠሩት ነጋዴዎች በመላው አፍሪቃ ነግደዋል። ጀበርቲዎች ያረብ ክልሶች ሲሆኑ በሐረር፣ በታጁራ፣ ዘይላና በርባራ ሰፍረው ነበር። በአፍሪቃ ቀንድ የጀበርቲዎች ታሪክ ከ11ኛው ክፍለ ዘመን ሼህ ኢስማኤል ጀበርቲ የዳሮድ ሱማሌ ጎሣ ቅድማያት ከአረብያ ፈልሶ ሰሜን ምሥራቅ ሱማሌ ሰፍሯል። በአፍሪቃ ቀንድ ሰሜንና ምሥራቅ ጀበርቴዎች የባሪያ ንግድ ገበያውን በብቸኛነት ይዘው ያለምንም ችግር ለግብፅና አረቢያ እንዲሁም ለፋርስ ባሪያ አቅራቢዎች ነበሩ። የባሪያ ንግዱም በአብዛኛው ሕፃናትን በተለይም ልጃገረዶችን ይመለከታል። ሕፃናቱ የሚመጡበት አካባቢ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሲሆን የጋላና ሲዳማዎች አባቆሮዎች እነዚህን ሕፃናት የሚያገኙት ደካማ ከሆኑ ጎረቤቶቻቸውና በመካከላቸው ባለው ጦርነት፣ ባሪያ ፍንገላና አደን እንደነበረ የፒ ኢ ለቭጆይ ጥናት ያረጋግጣል።

ይህም፣

" The slave trade was largly a trade in children especially girls. The children were brought from regions south and Southwestern Ethiopia. The Galla and Sidama principalities obtained many of these children in slave raids on their weaker neighbours or in disputes between themselves. Many were kidnapped and some were purchased in times of famine. A distinction was made between the "red" and " "black" slaves." (P.E Lovjoy; *Transformation in Slavery; Cambridge: 1983, pp.149-150*)

ቀደም ሲል ጆን ኮምዴን የተባሉት " Abyssinia and its people " (ኑሮ በቴስ ዩሐንስ አገር) እ.አ.አ በ1868 ዓ.ም በለንደን ከተማ ባሳተሙት መጻሐፋቸወ ገጽ 194 ላይ የሚከተለውን አስፍረዋል።

" The slave trade is carried on by the **<u>Mohamedans</u>** alone. Chrstians buy for domestic purpose, but are not permitted to sell, and the penality of death by hanging is affixed to the act of selling a christian child. The Gallas are solled by their despotic kings in the territories of Enarea and Djimma."

ባማርኛ፣

"የባሪያ ንግድ የሚከናወነው በእስላሞች ነው። ክርስቲያኖች ለቤት አገልግሎት የገዛሉ ለመሸጥ ግን አይፈቀድላቸውም። የክርስቲያን ልጅ የሸጠ ቅጣቱ ስቅላት ነው። ጋሎች የሚሸጡት በፈላጭ ቆራጭ ንጉሣቸው በጅማና እናሪያ ግዛት ነው።

" The southern most provinces of Galla, Enarea, Djimma, Goma and others are governed despotically by their several chiefs and supply by arbitrary coercion slaves for the Turkish market . "

ትርጉሙ፣

" በደቡብ ዳር የጋላ ክፍለ አገሮች እንደ እናሪያ፣ ጅማ፣ ጎማና ሌሎቹም የሚግዙት በፈላጭ ቆራጭ አባቆሮዎቻቸ ሲሆን እያስገደዱም ለቱርክ የባሪያ ገባያ አቅራቢዎች ናቸው። "

ኮምዴን ዘገባቸውን ቀጥለው በገጽ 201 ላይ የሠፈረው፣

**" The Gallas of a district named Follo pay a heavy tax to the king of Djimma, for the permission to purchase boys and prepare them as eunuchs for the Turkish harmes."**

ባማርኛ፣

" በፎሌ ወረዳ የሚኖሩት ጋሎች ወንደ ልጆችን እየሰለቡ ማለት ጃንደረባ እያደረጉ ለቱርክ ገበያ ለማቅረብ ፈቃድ ለማግኘት ለጅማው ንጉሥ ከባድ ግብር ይከፍላሉ። "

በደቡብና ምሥራቅ ኢትዮጵያ ከዛሬ መቶ ሠላሣ ዓመት በፊት የነበረውን እጅግ በጣም ዘግናኝ ሁኔታ ከፍ ብሎ ሐቀኞቹ የመዘገቡትን ስናገናዝብ፤ ዛሬ እንደ እቶ ቡልቻ ደመቅሳና "የጎሣ ነፃ አውጭ ግንባር" ነንባዩችን መቀዣበርን ከሥር መሠረቱ ለማጋለጥ እንሆ ያለምንም ይሉኝታ ሐቁን ለማወቅ ዕድል ላልገጠማቸው ወገኖቻችን ለማሳወቅ መንፈሳችን በከፍተኛ ትጋት ይነሳሳል።

የሸዋው አጤ ምኒልክ " መሬታችንን ቀማን፣ የገዳ ባሕላችንን አጠፉብን፣" <u>ዴሞክራሲያዊው የገዳ ሥርዓት</u>" እድገቱ ተጨናገፈብን፣ የነፍጠኞች " ባሪያ " ተደረግን ወዘተረፈ. እያሉ የውሸት እምቢልታ የሚንፉት ሁሉ ሰምተው በድርጊታቸው ይፈሩ። በጥቁር ሕዝብ ጠላቶች ዘረኛ ፈረንጆች ፀረ-ኢትዮጵያ ስብከትና ቅስቀሳ ተግተው ላይና ታች የሚሉ ቅጥረኞች አደብ ገዝተው ወደ ሕሊናቸው ተመልሰው ማስተዋል ይችሉ ዘንድ ሐቁ ይኸውላቸው።

የባሪያ ሥርዓት በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሌላው ዓለም እንደነበረው ሁሉ ከአክሱም መንግሥት ዘመን በፊትም ሆነ በኋላ ነበር። በመካከለኛው ዘመን ይልቁንም በደቡብ፣ በመሓልና ምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት በይፋት፣ በሃድያ፣ በባሌ፣ በዘይላ፣ በአዳል፣ በደዋሮ (ሐረርጌ) ወዘተ እስላማዊ ሡልጣናት እንዲሁም በአእማዊዎቹ የጅንጃሮ፣ የሱጋሞ፣ የዳሞት፣ የጎንጋ ወዘተ. ማኅበረሰብ ባሪያ ፈንጋዩች ነበሩ። ይህንንም ሁኔታ ታዋቂ የአረብ የጅኦግራፊና የታሪክ ሊቃውንት እነ እድሪስ ኢበን ሀኩል፣ ማሱዲ፣ ኢበን ባቱታ፣ ማቅሪዝ ወዘተ. በሰፊው መዝግበውታል። በተለይም አልማሪ (በ1335ዓ.ም)፣ ማቅሪዝ (በ1430ዓ.ም) የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ እስላማዊ ግዛቶችን ማለት የሃድያን፣ የደዋሮን፣ የአራባቢኒ፣ የይፋት፣ የሽርካ፣ የአዳል ዘይላን አስመልክተው በተለይ ደግሞ በሃድያ ሡስጥ ብዙ ባሮች ከየቦታው እንደሚወሰዱና ጃንደረባ ተደርገው በዘይላ ወደብ በኩል ለአረብ ገበያ ይልኩ እንደነበረ ተመዝግቧል። <u>ወሸሉ</u> ከተባለ ቦታ እየተሰለቡ ለገበያ ይቀርቡ እንደነበረ በጀርመንኛ የተደረገውን ጥናት ያገናዝቧል፣

Nach Hadija stroemen sehr viele Sklaven und Eunuch zusammen. Verschnitten wurden aber in der Stadt ***<u>Washellu</u>*** gemacht, da dies in Abeessinien verboten sei, und Washelu die einzige Stadt sei, wo dies geschehen duerfe. (P.Paulischke Adal-Laender 1884 Leipzig, p.17)

ባማርኛ፣

አያሌ ስልብ ወይም ጃንደረባዎች ወደ ሃድያ ይጎርፉሉ። የሚሰለቡት ግን በወሸሉ ከተማ ነው፣ በአበሾች ዘንድ የተከለከል ስለሆነ በወሸሉ ብቻ ነው ይህ ድርጊት ሊከናወን የሚቻለው።

የይፋት ወላስማዎች አዳል ሱልጣናት ከሸዋ ወደ አውሳና ሐረር ተዛውረው በ1445 ዓ.ም ሐረርን ቆርቁረው የባሪያ መነገጃ ዋና ማዕከል አድርገዋት፤ ለኢትዩጵያ አጤ መንግሥት ሳያመቻቸው እየገበሩ፣ ሲመቻቸው እያመጹ የሃይማኖት ጦርነት ጅሃድ ሲያካሂዱ እንደነበረ ይታወቃል።

ስለሆነም ዳግማዊ አጤ ምንይልክ በምሥራቅ ይሁን በደቡብ ምዕራብ የጥንት ኢትዩጵያን ክፍለ ሀገራት በምሥራቅ የአዳልና የደዋሮን (ምዕራብ ሐረርጌን)፣ ባሌን፣ ሃድያ ከምባታን፣ እናሪያ (ከፉ ኢሉባቦር)፣ ዳሞት (ወለጋ)፣ ፈጠጋር (አሩሲ)፣ ወዘተረፈ. በከፊል ለማስመለስ ያደረጉትን ተገቢ ዘመቻ በተለይ የኦነግ ጀሌዎች "የገዳ ዴሞክራሲዊ ሥርዓትን" ለማጥፋት የተደረገ መስፋፋት ነው እያሉ ይቀሳፍታሉ። የሱማሌ እስላማዊ ጎሣዎች አረብ ነን ብለው በአበሻ ሕዝብ ጥላቻና በጸረ ክርስትና የጅሃድ ጦርነት የመስፋፋት ሴሜት ከአቅማቸው በላይ ተወጥረው በጸረ ኢትዩጵያነት ተሰልፈው የእንግሊዝና ጣሊያን ቅጥረኛ ባንዳ ተላላኪዎች መሆናቸውን አስመስክረዋል።

እነ አቶ ቡልቻ ደመቅሳና ብጤዎቻቸው ጥቂት የወለጋ፤ የጅማና አካባቢው ጠባብ ጎሠኞች የቅርብ ዘመን መጤ ሰፋሪዎች ውላጅ መሆናችሁን ማሳወቅ ግድ ይላል። በደቡብና ምዐራብ የባሪያ ሥርዓተ ማኅበር ተስፋፍቶና አብቦ የነበረበት እንጂ የዘላኖች መደብየለሽ የጋራ ስሪት በወለጋና ጅማ ፈጽሞ አልነበረም።

በመጀመሪያ ዛሬ ወለጋ ጅማ፤ ኢሉባቦር፣ ወሎ፤ አሩሲ ወዘተረፈ. በሚባሉት ክፍለ ሁገራት ውስጥ ከጋላ የመስፋፋት ወረራና ዘረፋ በፊት ጥንታዊው ያማርኛ ስማቸው ዳሞት፤ እናሪያ፤ ቢዛንሞ፤ ጎንጋ፤ ጋፋት፤ ዝሆን ዱር (ጅባትና ሜጭ ያ)፤ቤተ አምሓራ (ወሎ) ተብለው የሚጠሩ እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ።

የጋላ ሜጭያ ወራራ ጎሣዎች የእናሪያን ነባር ሕዝብ እስከ 1840 ዓ.ም ድረስ ሲጨፈጭፉት እንደነበር ለምን የነፃ አውጭና የብሔር ጭቆና አቀንቃኞች ዝምታን መረጣችሁ? ደግሞስ በጥቅሉ የጎንጋ ሕዝብ በመባል የሚታወቁት የዳሞት፤ የጋፋት፤የእናሪያ፤ የየም፤ የገቦ፤ የሻካ፤፤ የሽናሻ፤ የቢዛንሞ፤ የእንፌሎ፤ ወዘተረፈ ጥንታዊ ነባር ሕዝብና የዳበሩ ያካባቢ መንግሥታት የት ደረሱ? ከነአቶ ቡልቻ መልስ እንጠብቃለን።

<u>ዳሞት</u> በጉራጌና አባይ ወንዝ መካከል ያለው አገር ከአጤ አምደ ጽዩን ከ1314 ዓ.ም ጀምሮ የኢትዩጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አካል እንድሆነ የተረጋገጠ ነው። የዳሞት ሕዝብ በ17ኛው ክፍለ ዘመን ከወራሪው የጋላ ሜጭያ ጎሳ ጋራ እስከ 18ኛው ክ.ዘ ድረስ ተዋግቶ ተሸነፈ። ከእልቂቱ የተርፈው ከፊሉ ብቻ እአባይን ተሻግሮ ወደ ጎጃም ሸሸ። ጥቂቱም ደግሞ ወደ ሸዋ ከምባታ፤ ጉራጌ፤ ምንጃር፤ ተጉለትና ቡልጋ፤ መራ ቤቴ ነባር ሕዝብ ዘንድ ተስደው በየአምባውና ሸለቆው ሰፈሩ። እጅግ በጣም  ጥቂቶች ደግሞ ጋላ ሆነው ቀርተዋል።

<u>የእናሪያ</u> ሕዝብ በደቡብ ምዕራብ ኢትዩጵያ ከጎንደር ማዕከላዊ መንግሥት ተቆርጦ  ለነፃነቱ ብቻውን በከፍተኛ ጀግንነት ለረጅም ዓመታት እስከ 1840ዎቹ ድረስ ተዋግቶ ከተሸነፈ በኋላ ነው በዚሁ ስፍራ የጊቤ መንግሥት የተባሉት የሊሙ፣ የጉማ፤ የጎማና የጅማ መሳፍንት መንግሥት የተመሠረቱት። አነዚህም ባሪያ አሳዳሪና ፈንጋይ የነበሩ ናቸው። በባሮን ዴዴሳ ወንዞች መካከል ወረው የሰፈሩት አራቱ የቢሎ ሌቃ፤ የኖላና፣ ይረሃና ሜጭያ (አረፉ ኦሮሞታ) እንዲሁም ከፍ ብሎ የተጠቀሱት አራቱ የጅማ፣ የጉማ፤ ጎማና የሊሙ ሜጭያ እስላማዊ ንዑስ መንግሥታት (አረፉ ነጋዶታ) የተሰኙት ዘወትር በጎሳ ወሰን ጦርነት የሚጨራረሱ ባሪያ ፈንጋይና ያካባቢው ባሪያ ነጋዴዎቹ አክፋላ የተሰኙት እንደነበሩ በ1845 ዓ.ም ሁለት እንግሊዛውያን ለግማሽ ዓመት ያህል በአባይና በላይኛው ጊቤ ወንዝ አካባቢ ያለውን አገር ጎብኝተው ሲመለሱ ያቀረቡት ዘገባ ያስረዳል። በተጨማሪም ቀደም ብሎ የተጠቀሰውን የሌላው እንግሊዛዊ ጆን ከምዴን ሆተን እ.አ.አ በ1868 ዓ.ም በለንደን ከተማ ባሳተሙት መጽሐፍ Abyssina and its People  ገጽ 194 ላይ የሳፈሩትን ያገናዝቧል።

# <u>ከለንደን ሹመት መልስ</u>

ወታደራዊ ደርግ ያጤውን መንግሥት ገልብጦ፤ 17 ዓመታት ሕዝቡን  በአብዩት ስም ሲያሽብርና ሲመዘብር የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መሠረት አጥፍቶ፣ ታላላቅ አርበኞችንና ባለሙያ ኢትዩጵያውያንን ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ፈጅቶ፣ ለጥቁር ጣሊያን የፋሽስት ሙሶሎኒ ሙት መንፈስ ልጆች ለሆኑት የምዕራባውያን ቅጥረኞች ለነ ወያኔ ሕወሐት፤ ሻዕቢያና ኦነግ ጥርጊያ መንገዱን አዘጋጅቶ፣ በአሜሪካ መንግሥትና ተባባሪዎቿ ለንደን ለይ በተደረገው የይስሙላ ስብሰባ ተሳትፎ፤ ሠራዊቱ በጠቅላላው ትጥቁን ፈቶ እንዲበተን አዞ ወደመ። የኢትዩጵያ የግዛት አንድነትና ልዕላዊነት ከለንደኑ የግንቦት ወር 1983 ዓም. ስብሰባ ማለቅ ጋራ አብሮ አክትሟል፡

ቀጥሎም በሰኔ ወር በአዲስ አበባ የሽግግር መንግሥት ተብዬ ለመመሥረት ተብሎ ጉባዔ ተደርገ። ከስብሰባው ዋና ተካፋይና ተዋናኝ አንዱ ኦነግ ነበር። ብዙ ተለጣፊና አፍቃሪ ወያኔ ሻዕቢያ የነበሩ የጎሳ ድርጅቶች ብቻ ተጠርተው ኢትዩጵያን በጎሳ ለመከፋፈል አስቀድሞ የተቀደውን ለማጽደቅ መሰብሰባቸው ይታወሳል። ይህንንም ሂደት የተከበሩ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ "ኦነግ ወያኔ ኢሕአዴግ አጅቦ አዲስ አበባ መግባቱና የሽግግር መንግሥት መሥራች አካል መሆኑ ለኦሮሞ ሕዝብ አንድ ርምጃ ወደፊት እንዲሄደ ይገመታል" በማለት ተርከዋከል።

አዎ! ኦነግ በሰኔ ጉባኤ ላይ የኤርትራን ክፍለ ሀገር የመገንጠልና ቀሪውንም የኢትዩጵያ ሕዝብ ርስ በርስ አቃርኖ ለመከፋፈል ያውሮፓ ቅኝገዥዎች ረቂቅ ስልት የሆነውን የብሔር ብሔረሰብ መብት የራስን እድል በራስ መወሰን እስክ መገንጠል መብትን ያረጋገጠ ቻርተር ሲጸድቅና የሽግግር ምክር ቤት ሲቋቋም ዋና አጃቢና አቃላጭ አስፈጻሚ ነበር። በጉባኤው ላይ ኦነግ በሚሲዎን ቀለብ ሰፋሪዎቹና የበላይ ጠባቂዎቹ ታጅቦ ባማርኛ አልናገርም የምናገረው በጌቶቼ ቋንቋ በእንግሊዘኛ ነው ብሎ ሲኮላተተፍ ወያኔዎች ባማርኛ ተናግረው ጉድ ማድረጋቸውን ፕሮፌሰር መራራ ጉዴና ለጦቢያ መጽሔት ገልጸዋል። ወያኔ ኢሕአዴግ አብዛኛውን ቁልፍ ሹመት ማለትም የፕሬዘዳንት፤ የጠቅላይ ሚኒስትር፤ የወጪ ጉዳይ፤ የመከላከያና ያገር አስተዳደር ሁሉ ሲወስድ ኦነግ ድጋፉን ሰጥቶ ከማጨብጨብ በስተቀር ምንም ፋይዳ አልነበረውም።

ኦነግ ሳደረገው አጃቢነትና ተባባሪነት የወያኔንና ሻዕቢያን ሙሉ ፈቃድና ስምምነት አገኘ። ከተለጣፊው ኦሕዴድ አጋሩ ጋራ በመሆን በአማራው ሕዝብ ላይ የጎሳ ማጽዳት ዘመቻውን በሰፊው አቀነባበረ የኦነግና ኦሕዴድ ድርጅት መሪዎች ምንም ጊዜ የሚያሰጠይቃቸው ከፍተኛ ወንጀል ፈፅመዋል። በብደኖ፤ በአርባጉጉ፣ በአሰቦት፤ በአሶሳ፤ በምሥራቅ ወለጋ ወዘተረፈ በአረመኔነት የተጨፈጨፉት አማሮች ደም ፈሶ ከቶ አይቀርም።

ይህን በተመለከተ የሃደያው ተወላጅ የተከበሩ አቶ ሃይሌ አርፌቾ(ነፍሳቸው ትማር) ሲጽፉ የ"ኦሮሚያ" ጉዳይ በደቡብ ኢትዩጵያ ሰላም እንዳይሰፍን የሚያደርግ ሁኔታ እየፈጠረ መሆኑን ደጋግመው አብራርተዋል።

በአጠቃላይም ወያኔ በ1983 አዲስ አበባ ዘምቶ በብቸኛዋ ልዕለ ኃያል አሜሪካና እንግሊዝ መልካም ፈቃድና ትብብር በጠመንጃ ኃይል ሥልጣን ኮርቻ ላይ ከተፈናጠጠ ጀምሮ በደቡብ፣ ደቡብ ምሥራቅና ደቡብ ምዕራብ ኢትዩጵያ የዘር፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የወሰን ግጭቶች እንዳላቋረጡና በዚህም ሳቢያ የብዙ ኢትዩጵያውያን ሕይወት እንዳለፈ፣ በብዙ ሚሊዎን የሚቆጠር ንብረት እንደወደመ ገልጽዋል።

በተለይ ያሩሲ አርባ ጉጉን አረመኔያዊ ጭፍጨፋ በመጥቀስ ከዐማርኛ ተናጋሪው ሌላ የሃድያ፣ የከምባታ፣ የወላይታና የጉራጌ ተወላጆች በግፍ እንደተገደሉ አስታውሰዋል። ከዚህም ጋር በማያያዝ ሲያስረዱ፣

"የዛሬይቱ ኢትዩጵያ ሕዝቦች በረጅም ታሪካቸው፣ በሰላም በጦርነት በንግድ በጋብቻ አንዱ ከሌላው እየወሰድ ያዳበሩት ኢትዩጵያዊ እሚያሰኝ የባሕል፣ የሥነ ልቡናና የቋንቋ መለያ አፍርተዋል።

በሌላ በኩል ሲታይም ደግሞ የዛሬው የኢትዩጵያ ሕዝብ የቋንቋ ክፍፍል፣ በዘር ላይ የተመሠረተ አይደለም። ለምሳሌ የዛሬዎች የአርሲ ኦሮምኛ (ጋሊኛ) ተናጋሪዎች ብዙዎቹ የሃድያ ተወላጆችን የሚያጠቃልሉ ናቸው። እንደ ዕውነቱ ከሆነ በአርሲ እስከ ሁለት ሚሊዎን ይደርሳሉ ተብሎ የሚገመተው የሃድያ ተወላጆች በቁጥር ከኦሮሞ የሚወለዱትን ይበልጣል። የዛሬ 370 ዓመት ከተፈጸመው የወረሞ ወይም ጋላ ወረራ በፊት የሃድያ ግዛት ሰፊ የሆነ ከስምጥ ሸለቆ ሐይቆች (ዝ ይ፣ አዋሳ፣ ላንጋኖ፤ ሻላ፣ አቢያታ፣ ጨው ባሕር) በግራና በቀኝ የሚገኝ፣ ሸዋ፣ ባሊና ሲዳሞን የሚያዋስን ነበረ። " ብለዋል። ይህንንም ለማረጋገጥ የዘር የቋንቋ የሃይማኖትና የባሕል ጥናት ባለሙያ ጀርመናዊው ተመራማሪ ኡልሪህ ብራውካምፐር ስለ 17ኛና 18ኛው ክፍለ ዘመን የሃድያ ግዛት ያቀረቡትን ጽሑፍ ጠቅሰዋል። (Die Geschichte der Hadya in Süd-Aethiopien) እኝህ ተመራማሪ እንደጻፉት፤ ከአዋሽ እስክ ገናሌ ወንዝ፣ ከዝ ይ እስከ ዋቢ ሸበሌ ባለው በዛሬው አሩሲና አካባቢው ሁለት ዓይነት ባሕል ጎን ለጎን ሲያድጉ ቆይተዋል። በአንድ በኩል በቁጥር አነስተኛ የሆኑት የጋላ ገዳ ሥርዓት ና ሃይማኖት ተከታዩች፣ በሌላ በኩል ሁለት ሦስተኛ የሚሆነው በቁጥር ከፍተኛ የሆነው የሃድያ ሕዝብ በአብዛኛው የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ነበሩ። "

ይህ የዛሬውን የወያኔና የ "ኦሮሚያ ነፃ" አውጭዎችን የዘር ፕሮፓጋንዳና ክልል የሚቃረን በመሆኑ ወያኔና ኦነግን የሚያስቆጣ ቢሆንም አሌ የማይባል ሐቅ ነው ሲሉ አቶ ሃይሌ አርፌቾ ተናግረዋል። በመቀጠልም ይህም ሁኔታ ሃድያን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን የብዙ የደቡብ ምሥራቅና ደቡብ ምዕራብ የኢትዩጵያ ብሔሮችን የታሪክ ሂደት የሚያረጋግጥ ነው ብለዋል። በመሆኑም ዛሬ በሚሊዎን የሚቆጠሩ ኦሮምኛ ተናጋሪዎች የራሳቸው ያልሆነ ከውጭ በግዳጅ የተቀበሉትን ቋንቋ ስለሚናገሩ፣ ወያኔ ዘርና ቋንቋን አንድ አድርጎ "ክልል" እያሉ

ኢትዮጵያን በልበ-ወለድ ጎሣዎች ሸንሻኖ እንደ ፋሽስት ጣሊያን የሚያስተዳድሩበትን ዘይቤ በአጽንኦት ተቃውመዋል። የግዳጅ ጎሣና ቋንቋ ፖለቲካ ውጤት ደግሞ እንደምናየው የማይቋርጥ ግጭትና ደም መፋሰስ ነው በማለት አረጋግጠዋል።

# የገባር ማደሪያ

የኦነግ ነፃ አውጭ ተብዬዎች፣ አገር በቀል ጠባብ ጎሠኛ የፈረጅ አፈቀላጤ የኢትዮጵያ ምሁር  ነንባይ ድንብርብሮች ሁሉም በጅምላ  ሲሰሙትና የሚያሰሙት ማደናቆሪያ ያማራ ነፍጠኛ ገባር ማደሪያ ስሪት በምኒልክ ዘመን በደቡብ ተስፋፋ አያሉ ነው።

በቅድሚያ ገባር ማደሪያ ከባሪያ አስዳሪዎቹ ከደቡብና ምዕራብ ማለትም ከጅማ፣ ከጉማ፤ ከሊሙ ወዘተረፈ ፈጽሞ የተለዩ ነው።

በዓለም ላይ በይተኛውም ስፍራ መንግሥታዊ ድርጅት ያለው ማኅበረሰብ ከዜጎቹ ሁሉ ግብር ይቀበላል፤ ቀረጥ ይሰብስባል። በመሆኑም በኢትዮጵያ ገባር ማለት ለመንግሥት ግብር የሚከፍል ዜጋ ማለት ነው። የግብሩ ዓይነት ደግሞ የጉልበት፤ የዓይነት፣ የገንዘብና ሌላም ዓይነት ሊሆን ይችላል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መሠረት እርሻና ከብት ርባታ ናቸው። ግብር የሚከፈለውም ከነዚህ ምርት ውጤቶች አሥራት በማውጣት ነበር።ኢትዮጵያ የብዙ ነገዶችና ማኅበርሰቦች አገር ስለሆነችና ነጻነቷንና ልዑላዊነቷን በዜጎቿ የጋራ መስዋእትነት አስከብራ ብዙ ሺህ ዘመናት የኖረች አገር ናት።

የተለያዩ ነገዶችና ማኅበረሰቦች ለአጤው የሚከፍሉት ግብር ዓይነትና መጠን እንደ ባሕሉና አካባቢው የተለያየየ ነበር።

የገባር ማደሪያን ፈረንጆችና አገር በቀል ምልምል ሊሂቃን እንበለ ዕውቀት ከአውሮፓ ፊውዳላዊ ሥርዓት ጋራ አቆራኝተው የማጥላላት ሰፊ ዘመቻቸውን አሰራጭተዋል።

ዳሩ ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ያውሮፓውያን አይነት ፊውዳላዊ ሥርዓተ ማኅበር አልነበረም። በዘር ግንድ የሚተላለፍ ጉልትና መደብ በኢትዮጵያ አይታወቅም። በገበሪና አስገባሪው መካከል የመደብ ሆነ የባሕል ልዩነት የለም። በአበሻ ሕዝብ ባሕልና ልማድ ባላባት ማለት አባት ያለው፤ ከጨዋ የተወለድ፤ ከባሪያ ያልተወለደ ማለት እንጂ የመሬት ከበርቴ ወይም ፊውዳል ማለት አልነበረም። በአውሮፓ በጀርመን፤ በፈረንሳይ፣ በጣሊያን፤ በእንግሊዝ ወዘተረፈ ዛሬ ያለው የግል መሬት ይዞታ ስሪት ከፊውዳላዊው በቀጥታ የወረዳና የቀጠለ ነው።

የፊውዳል ውላጅ ዘርያዎች ሰፋፊ ይዞታቸውንና ምሽግ ታላላቅ ቤቶቻቸውን በመንከባከብ ከትውልድ ትውልድ ያስተላልፋሉ። መታወቅ ያለበት ሐቅ አለ። በአፍሪቃ አህጉር ከአውሮፓ ፈረንጆች የተለየ ብቸኛ ነጻ መንግሥትና ማኅበራዊ ሥርዓት፤ ሥልጣኔ፣ የክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ በመኖራቸው እነዚህም የኢትዮጵያን ሕዝብ ለአያሌ ዘመናት ከውጭና ከውስጥ የተቃጡትን አረፍራሽ ሁኔታዎች ተከላክለው ለማቆየት ማስቻላቸውን ጠንቅቀው ስለተረዱ እነዚህን ተቋማት በማንኛውም መንገድ በማስጠፋት ብቻ የነሱ ጥገኛ ተገዥ ማድረግ እንደሚቻላቸው አስበው በግልጽና በስውር ጦርነት ከፍተው ያልሞከሩት ነገር ከቶ አልነበረም።

በኢትዮጵያ በገባሪና አስገባሪ መካከል የነበረው ግንኙነት ፈረንጆች ከውጭ ሰምተውና በፀረ ኢትዮጵያ ምቀኝነትና ጥላቻ ስሜት እንደተረኩት በጭራሽ ሳይሆን እንደ አካባቢው ሁኔታ በጋራ ጥቅምና መተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ነበር።

ለምሳሌ ያህል የጌራ ባላባት የነበረችው ወይዘሮ ገኒ ጉምቴ ለአጤ ምኒልክ የምትከፍለው ግብር ኩታና ጋቢ ነበር። ምኒልክ ጥር 4 ቀን 1889 ዓ.ም ለወይዘሮ ገኒ ጉምቴ በጻፉት ደብዳቤ

የሰደድሽልኝ መተያያ አንድ ድርብ፤ አንድ ኩታ ደርሶኛል። እጅግ ማለፊያ ነው። እግዚአብሔር ይስጥልኝ። ነው። እማርስበት በሬ ያልሽውንም ከእእባ ጅፋር ዘንድ እሥር በሬ ዳርጌሻለሁ። (ጳውሎስ ኞኞ: *አጤ ምኒልክ* 1984 ገጽ 36)

# የትናንቱ መሬት ላራሹና የዛሬው ዓለም አቀፍ መሬት ቅርምት

በአጤው ዘመን የተማረው ኃይል በልምዱና ጠቅላላ አስተሳሰቡ በውጭ ትጽእኖ ርዕዩት የሚመራና የሚተራመስ ነበር። ተማርኩ ባይ ቅጥረኛ የኢትዩጵያን አጤ መንግሥት ለመጣል በጠላትነት እንጂ ተዛባ የተባለውን የፍትሕና አስተዳደር ለማቃናት ከቶ አልነበረም። በመጀመሪያ ደረጃ የአንድ ማኅበርሰብን ዕድገት ለመለወጥ በከፍተኛ ሀገራዊ ስሜትና ፍቅር የማኅበረሰቡን ታሪክና አጠቃላይ ሁኔታ ከስር መሠረቱ ጠንቅቆ ማወቅን ይጠይቃል። ነገር ግን ተማረ የተባለው ወገን በመልኩ እንጂ በሃሳቡ ኢትዩጵያዊ ያልሆነ ፈጽሞ በማይገባው ቋንቋ በእንግሊዘኛ ወይም በፈረንሳይኛ የቃል ጥናት ድግምት እንደ በቀቀን ሰምቶ አስተጋቢ ከመሆኑን ሌላ ከተለያዩ አገራት በመጡ የውጭ አስተማሪ ተብዬ ሰላይ ወኪሎች የባሕልና የኢኮኖሚ ተጽእኖ አስፋፊ መልክተኞችና ሚሲዎኖች ተኮትኩቶ ያደገ ነበር። ለከፍተኛ ትምህርት ተብሎ በተለያዩ የአውሮ አገራት የተላከውም ቢሆን የሄደበትን አገር ልብለብ ስልጠና ተሰጥቶት ያየውንና የተነገርውን ለቃቅሞ ውክልናውን ሊያስፈጽም ይመለሳል።

በዘመናዊ ትምህርት ሽፋን የተደራጃው አገር በቀል ቅጥረኛ መደብ በውሸት ሾሻሊዝም ካባ ተጀቡና ሲንበላጠጥ፤ የኢትዩጵያን ማኅበረሰብ ፊውዳል ብሎ የሰማውንና የተነገረውን ሁሉ እየጠቀሰ ማርክስና ሌኒኒ እንዳሉት እያለ የማስመሰል ትርኢት ፈጻሚ ጠጣ ትውልድ ነበር። በኢትዩጵያ ውስጥ የተለያዩ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች ለብዙ ዘመናት አብረው እንዳልኖሩ ሁሉ ተማርኩ ባዩ ቅጥረኛ ኢትዩጵያ የኅሳዎች እሥር ቤት ናት አለ። ኢትዩጵያን ቅኝግዛታቸው ለማድረግ የወረሩት ፋሽስት ጣሊያኖች ይነዙት እንደነበረው ፕሮፓጋንዳ ዐማራው ሕዝብ በጨቋኝነት ሌሎቹ ኅሳዎች በተጨቋኝነት ተፈረጁ። በዘመኑ ፈሊጥ የብሔር የራስን እድል በራስ መወሰን መብት እስከ መገንጥል ተሰበከ። የዚሁ መፈክር ዋና ዓላማ በሰሜን በስንት የፖለቲካ ትግል የተመለሰችውን የኤርትራን ክፍለ ሀገር ለማስገንጠል፤ በምሥራቅ ኢትዩጵያ ከአዋሽ ወንዝ በመለስ ባሌንና አሩሲን ጨምሮ ከሱማሌ ጋራ በማዋሃድ የቅኝ ገዥዎች አሸንጓሊትና ሞግዚት በመፍጠር ቀይ ባሕርና የአፍሪቃ ቀንድን ቁልፍ መስመር ለመቆጣጠር ነበር።

አንደ ፈሪሳውያን አነብናቢው፣ ርስ በርሱ እንኳን የማይደማመጠውና ኢዲሞክራሲያዊ እኔ ብቻ የማርክሳዊና ሌኒናዊ ቅኖና ሊቂ ባይ የፈላጭ ቆራጭ ሥልጣን ጥመኞች ዋና ማወናበጃ <u>መሬት ላራሹ</u> የተባለው መፈክር ነበር። ከቬትናም ጸረ ቅኝ ግዛት ተዋጊ አርበኛ ሆችሚን የተገኘውን መሬት ላራሽ መፈክር የኢትዩጵያ ግራ ተብዬ ድንብርብርና አስመሳይ ለተማሪው እንዲያስተጋባ አስደርገው በዘመነ ደርግ ገበሬውን የርስት ስሪቱንና የግል ሃብት ይዞታውን ቀምተው በመላው የመንግሥት ጭሰኛ እንዲሆን አስገደዱት።

ከዚሁ ጋራ ተያይዞ በሰፊው ሲነዛ የነበረው በሬው ላም ወለድ ጭሰኘው ለባለ መሬቱ <u>ከሰባ አምስት በመቶ በላይ</u> ይከፍላል የተባለው ነበር። በየትኛውም ክፍለ ሀገር ይህ ዓይነት ክፍያ አልነበረም። ፍጹም በተቃራኒው ባለርስቱ የሚያገኘው እንደ አካባቢው የእርሻ መሬት ሁኔታ ማለትም ለምና ጠፍነት ርቦ፤ ሲሶ ሲሆን ማሳው ለም ከሆነ የእኩሌታ ወይም ግማሽ በግማሽ ነበር። ለመንግሥት ግብር የሚከፍለው ባለርስቱ ብቻ ነበር። በሰሜንና በመሃል አገር ጭሰኛ የሚባለው ቁጥር እጅግ በጣም ጥቂት ነው። የባለርስቱም ይዞታ በጣም ቁርጥራጭ አነስተኛ እንጂ በቂ ስፋት ያላው ባለርስት በተለይ በሰሜን አልነበረም። በውርስና የጋራ ይዞታ የሚከተለውን መሸንሸንና የመሬት ማነስ ችግር ለማስተካከል የተከበሩ አቶ በላይ አባይ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ በደርጉ ውስጥ ተሰብስበው በነበሩትና የተራማጅነት ጨንበል አጥልቀው የጠባብ ኅሰኝነት ዓላማቸውን በስውር ሲያራምዱ በነበሩት ልሂቃን ሴራ ተሰናከሉ።

ኢትዮጵያ አገራችን እስክ 1966 ዓ.ም ድረስ ምጣኔ ሃብቷ የፈረንጅ ከበርቴዎች ጥገኛ አልነበረም። ባለገሩ ሕዝብ ለኑሮው የሚያስፈልገውን ሁሉ እራሱ እያመረተ ለውጭ ንግድ አቅርቦትም መጠነኛ ችሎታ ነበረው። ይህን ሁኔታ ለመቀይርና የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በቀጥታ ለመቆጣጠር ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የእንግሊዝ፣ የጣሊያንና የፈረንሳይ ቅኝገዥዎች ከፍተኛ ምኞትና ሴራ ሲያውጠነጥኑ ነበር።

ቢቻል በዲፕሎማሲ ካልሆነም በጦር ወረራ ኢትዮጵያን ለመያዝ ይልፈነቀሉት ድንጋይ ከቶ አልነበረም። የዛሬው ያገራችን ሁኔታ ሲያያዝ የመጣ እንጂ የድንገት ክስተት ፈጽሞ አይደለም።

ደርግ ያለእግባብ የወረሰው ቤት ንብረት፤ ሃብት መሬት ለባለ ሃብቱ ሳይመለስ ወያኔ በትግሬ ክፍለ ሀገር ብቻ ሲመልስ በሌሎቹ ክፍለ ሀገራት አልተመለሰም።

ይባስ ብሎ ወያኔ ለሙና ሰፉፊውን የእርሻ መሬት ልአረብ፤ ለሕንድና ለቻይና፤ ለአውሮፓውያን በርካሽ ለ99 ዓመት ይቸበችባል። ገበሬው ከአነስተኛ ይዞታው ይፈናቀልቅል። ያረብና የሕንድ ቱጃሮች ደን እየመነጠሩ መሬቱንና ያካባቢውን የተፈጥሮ ሚዛን በማቃወስ ላይ ናቸው። ለውጭ ንግድ አበባ ተከላ የሚውለው መሬት በኬሚካል ተመርዞ በሰውና እንስሳት ላይ ከፍተኛ የጤና ጉዳት ደርሷል። በኢትዮጵያ የርሻ መሬት ቅርምትን በተመለከት ዓለም አቀፍ ተቃውሞ በያለበት ይሰማል።

ኢትዮጵያውያንን በቋንቋና በጎሳ አለያይተው ለበዝባዦች አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር በመመኘት በደቡብ አፍሪቃ ተወግዞ የተወገደውን የባንቱስታን አፓርታይድ ሥርዓት በቀለሙ፣ በዘሩ፣ በደም ትስስሩ፣ በእምነቱና አንድ በሆነው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የጎሣ ፖለቲካ እንዲሰፍን በቅጥር ነፍሰ ገዳዮች ተፈርዶበታል። "ዲሞክራሲ፣ የራስን በራስ ማስተዳደር እስከ መገንጠል፤ በራስ ቋንቋ በላቲን ቁቢ ፊደል መጠቀም" በሚባሉት ጨንበሎች የሚሸረበው ሴራ ሁሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ለውስጥና ለውጭ ጠላቶች መፈንጭያ ለማስደርግ እንጂ በእርግጥ ለሕዝቡስ ዘላቂ ጥቅምና እድገት ታስቦ እንዳልሆነ መታወቅ አለበት።

ፍትህ፣ እኩልነት፣ የሰብአዊ መብት መከበር፣ ዕድገትና ልማት በጎሳ በመለያየትናና በመገነጣጠል የሚመጡ ቢሆን ኖሮ ከማንኛው ሌላ አገር ይልቅ በቅድሚያ በተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶች (USA) ፣ በካናዳ፣ በጣሊያን፣ በፈረንሳይ፣ በእስፓኝ፣ በእንግሊዝ ወዘተርፈ. ውስጥ በተግባር ላይ መዋል

ነበረበት። ኤርትራም ከዘጠኝ የጎሳ ክልል አልተሸነሸነችም። የሱማሌ ልዩ ልዩ ጎሳ አባቆሮዎች ርስ ብርስ የሚጋደሉት፣ ይጎዝላቢያ የተበታተነችው፣ በላይቤሪያና በሩዋንዳ ያ ሁሉ ሕይወት ያለፈው በጎሳ ፖለቲካ ቅስቀሳ ነው። የዘረኞችና ከፉፉዎች የጎሳ ስሜት ስብከትና ቅስቀሳ ሥልጣን በአቋርጭ ለማግኘትና በቅጥረኛነት የባሕር ማዶ ጌቶቻቸውን ጥቅም ለማስከበር ብቻ እንጂ ለሕዝብስ ደንታ የለቸውም።

በኢትዮጵያ የግዛት ወሰን ውስጥ ያለው የትኛውም አገር፣ አውራጃ፣ ወረዳና ቀበሌ፣ የትኛውም ስፍራ የመላው ኢትዮጵያዊ ሕዝብ አንጡራ ሃብት እንጂ ለወረሞ፣ ለዐማራ፣ ለትግሬ፣ ለጉራጌ፣ ለሃድያ፣ ለሲዳማ፣ ለሱማሌ ወዘተ ነገድ ብቻ ተለይቶ የሚከለል በጭራሽ ያለመሆኑን ይወቁ። የባንቱስታን የጎሣ ክልል እንደ ደቡብ አፍሪቃ ተወግዶ ይቀበራል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በነፃና ዲሞክራሲያዊ ውሳኔና ይሁንታ ክፍለ ሀገራዊ ያካባቢ አስተዳደር ይመሠርታል።

በኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራዊ የራስ ገዝ ሥርዓት ከአክሱም ነገስታት በፊት ጀምሮ ያለ የነበረ የኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት መንግሥት ልዩ ታሪክና ባሕል ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ የፈረንጅ ርጥባን የጎሣ ፌደራሊዝም የድንጋይ ዘመን የጎሣ ፖለቲካ ሥርዓትን አሽቀንጥሮ ይጥላዋል።

ስለዚህ እንደ ወያኔ-ሻዕቢያና ኦነግ ወዘተ የመሳሰሉት ቅጥረኞች ፀረ-ኢትዮጵያ ተልዕኮ የዓለም ዘረኞች ሴራና ተንኮል ስለሆነ የጥቁር ዘር ሁሉ አውቆት ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ ማሳወቅ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ዜጋ ሁሉ ግዴታና ተግባር ነው።

**ገ, ሰንጎጎ ዘብሔረ ጋሞ** gelebewesengogo@yahoo.co.uk